**DSpace Institution**

**DSpace Repository** http://dspace.org

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2017-05

# þÿ ñ5 s*«Ê •ce ''ètÎô.5 +Õí'' ¥“ ' þÿG(6}'' pÍ”v} Í5%

þÿ ®•, u•u

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/17009

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

## ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋክልቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ - ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ ”የቴዎድሮስ ራዕይ” እና ”የካሳ ፈረሶች” ተውኔቶች ውስጥ


**በ**

**ሜልኮን ጌትነት**


**ግንቦት፣ 2017**

**ባሕር ዳር**

# ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ በ"ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ"የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ

**በሜልኮን ጌትነት**

**አማካሪ፡-**

**ዶ/ር ሂሩት አድማሱ**

**ሂዩማኒቲስ ፋክልቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፣**

**ድህረ ምረቃ ፕሮግራም**

**ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ በ"ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ"የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ**

**በሜልኮን ጌትነት**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

--------------------- ---------------------

**የአማካሪ ስም** **ፊርማ**

-------------------- -----------------------

**የፈታኝ ስም** **ፊርማ**

---------------------- ------------------------

**የፈታኝ ስም** **ፊርማ**

---------------------- --------------------

**ማረጋገጫ**

ይህ ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ በ"ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ"የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ በሚል ርዕስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ-ጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችን በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የጥናቱ አቅራቢ _______________

ፊርማ ______________________

የቀረበበት ጊዜ_______________

## ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት እንድማር እድሉን የሰጠኝን የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን አመሰግናለሁ። በመቀጠል መረጃዎችን በመስጠት፣ የኔን ስህተት በተደጋጋሚ በማረም ይህን ጥናት የተስተካ መልክ እንዲኖረው የረዳችኝን አማካሪዬን ዶ/ር ሂሩት አድማሱን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ሁሌም በማበረታታት፣ በማረም እና እንድጨርስ በመደገፍ ከጎኔ የነበሩትን ዶ/ር አንተነህ አወቀን ከልብ አመሰግናለሁ። እናቴ ሁሌም እንድማር ስለምታበረታታኝ፣ ብርታም ስለሆነች፣ ጥናቴን እንድጨርስ ከምትችለው በላይ ስለደከመች እናቴን አመሰግናለሁ፡፡ በተጨማሪ ይህን ስራ በምሰራበት ጊዜ "አይዞሽ" እያላችሁ ከጎኔ የነበራችሁ፣ ምክራችሁን የለገሳችሁኝ ጓደኞቼ እና ቤተሰቦቼ ሁላችሁም ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ማውጫ ገጽ


አጠቃሎ.........................................................................1

ምዕራፍ አንድ ........................................................................ 2

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................ 2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት........................................................................ 6

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች ........................................................................ 7

1.4. የምርምር ጥያቄዎች........................................................................ 7

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................ 8

1.6 የጥናቱ ወሰን ........................................................................ 8

1.7 የጥናቱ ዘዴ ........................................................................ 8

1.7.1 የጥናቱ ዘዴ (ስልት) ........................................................................ 9

1.7.2 ተውኔቶቹ የተመረጡበት መመዘኛ ........................................................................ 9

1.7.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................................................ 10

1.7.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................................................ 10

1.8 የምዕራፍ አደረጃጀት ........................................................................ 11

ምዕራፍ ሁለት ........................................................................ 12

የተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ.........................................................................12

2.1 የንድፈ-ሃሳባዊ ጽሁፍ ክለሳ......................................................... ....12

2.1.1 ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ........................................................................ 12

2.1.2 በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ እና በነባሩ ታሪካዊ ሂስ መካከል ያለው የታሪክ ግንዛቤ...... 14

2.1.3 የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ጭብጦች…………………………………………… 18

2.1.3.1. ርዕዮተ አለም…………………………………………………………18

2.1.3.2 የርዕዮተ አለም ቁልፍ ገጽታዎ…….……………………………… …… 19

2.1.3.1.3 ርዕዮተ አለም በስነጽሁፍ ሲተገበር…………………………………. 20

2.1.3.2 የሃይል ግንኙነት…………………………………………………… 23

2.2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ……………………………………………………25

ምዕራፍ ሦስት

3. ትንተና………………………………………………………………………… 28

3.1 የ”ቴዎድሮስ ራዕይ” ታሪካዊ ተውኔት አጽመ ታሪክ…………………………………28

3.2 ”የካሳ ፈረሶች” ታሪካዊ ተውኔት አጽመ ታሪክ……………………………………….29

3.3 ርዕዮተ አለም በተውኔቶቹ ውስጥ እንዴት ተንጸባርቋል……………………………….30

3.3.1 ”የቴዎድሮስ ራዕይ” ተውኔት ውስጥ …………………………………………….30

3.3.2 ርዕዮተ አለም ”የካሳ ፈረሶች”ውስጥ………………………………………………..34

3.4 ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ……………………………………………………………38

3.4.1 ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ ”የቴዎድሮስ ራዕይ” ተውኔት…………………………..38

3.4.2 ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ ”የካሳ ፈረሶች” ታሪካዊ ተውኔት ውስጥ………………..45

3.5 የኃይል ተለዋዋጭነት………………………………………………………………..47

3.5.1 የኃይል ተለዋዋጭነት ”የቴዎድሮስ ራዕይ” ተውኔት ውስጥ………………………47

3.5.2 የኃይል ተለዋዋጭነት "የካሣ ፈረሶች" ተውኔት ውስጥ……………………………..49

3.6 ዘመኑ በተውኔቶቹ ውስጥ ያሳደረው ተጽዕኖ..........................................50

3.7 የተውኔቶቹ አንድነት እና ልዩነት..................................................51

4. ማጠቃለያ..................................................................................... ....56

ዋቢ. መጻሕፍት....................................................................................57

# አጠቃሎ

*ይህ ጽሁፍ ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ በ"የቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ"የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ የሚፈትሽ ሲሆን ሁለቱም ተውኔቶች የዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስን ህይወት እና ትሩፋት በተውኔት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በእነዚህ ተውኔቶች ውስጥ የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ስነጽሁፋዊ ንድፈ ሃሳብ ጭብጦችን ርዕዮተ አለም፣ ማህበረ ፖለቲካ አውድን፣ የኃይል ተለዋዋጭነት እና ዘመኑ በተውኔቶቹ ውስጥ ያሳደረውን ተጽዕኖ ይፈትሻል፡፡ ተውኔቶቹን አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ "የቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ"የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ አጼ ቴዎድሮስ ሃገራዊ አንድነትን የሚያስጠብቁ እና የሚያዘምኑ ሰው ተድርገው መቀረጻቸው ተውኔቶቹን አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ሲሆን፣ ተውኔቶቹ ሁለቱም በተፈጠሩበት ዘመን የነበረው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ ዳራ ላይ መቀመጣቸው እና ያንኑ ዘመናቸውን ማንጸባረቃቸው የተለያዩ ያደርጋቸዋል፡፡ በጥናቱም ተውኔቶቹ በዘመኑ የነበረው የሃይል፣ ርዕዮተ ዓለም እና ማህበረ ፖለቲካዊ ሁነት የተንጸባረቀባቸው ሲሆን ይህ ጥናትም በተውኔቶቹ ውስጥ እንዴት እነዚህ ጭብጦች እንደተንጸባረቁ ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሥነጽሑፍ የሰው ልጅ ታሪክ እና የማንነት ጥያቄ በግልጽም ይሁን በስውር የሚነሳበት፣ የሚፈታበት፣ የሚገለጽበት ስፍራ ነው (Bennett እና Royle፤ 2004)፡፡ ሥነጽሁፍን ከሌሎች የኪነጥበብ ዘርፎች ከሚለዩት አብይ ምክንያቶች አንዱ ሕይወትን የሚያንጸባርቀውም ሆነ ምናባዊ የሆነውን ፈጠራ የሚያቀርበው በቃላት አማካኝነት መሆኑ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለባህል እድገት መሰረት የሆኑት ትውፊቶች፣ ሕዝባዊ ተረቶች፣ ዘፈኖች፣ ግጥሞች፣ ወዘተ... በጽሁፍ ተመልሰው ወደ ሥነጽሁፍነት በመለወጥ የሥነጽሁፍ ጥበብ ለመሆን በቅተዋል (አያልነህ ሙላቱ፣ 1997)፡፡

ተውኔት አንዱ የሥነጽሁፍ ዘርፍ ነው፡፡ ተውኔት የሚለውን ቃል የመጨዋወት፣ የመነጋገር፣ በአጠቃላይ ንግግር ጠቀስና አካላዊ ተሳትፎ ያለበት ተግባቦት ነው (የሻው፣ 1998):: ተውኔት በጊዜ ሂደት ከተራ ቃልነት አልፎ የእንግሊዝኛውን ድራማ ሊተካው ችሏል፡፡ ምክንያቱም ድራማ የሚለው ቃል በጥሬ ትርጉም ከመተግበር ወይም ከማድረግ ጋር የተያያዘፍች አለው፤ በግሪኩም "draein" ማለት "to do" ማለት ነው፡፡ (የሻው፣ 1998)፡፡ ከዚህ አንፃር ተውኔትና ድራማ ተወራራሽ ናቸው። በተዉኔት ውስጥ የተለያዩ ታሪኮችን፣ ስሜቶችንና ጭብጦችን የሚያሳዩ የተለያዩ ዘውጎች አሉ፡፡ እነዚህ ዘውጎች በተገለጹበት መንገድ እና በሚፈጥሩት ስሜት ይለያያሉ፡፡ ከተውኔት ዘውጎች መካከል ትራጀዲ (አሳዛኝ)፣ ኮሜዲ (አስቂኝ)፣ ሮማንስ (የፍቅር)፣ ሂስቶሪካል (ታሪካዊ) ተውኔቶችን ለአብነት ማንሳት እንችላለን፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ታሪካዊ ተውኔት ላይ እንደመሆኑ ስለ ታሪክ እና ተውኔት ትስስር እንመልከት፡-

> ታሪክ የሕዝብ፣ የተከታታይ ትውልዶች ሥራ፣ ኑሮ፣ ትግል፣ ተጋድሎ ነው። እያንዳንዱ የቀደመው ትውልድ ኀብረቱን፣ ንብረቱንና መብቱን በአጠቃላይ የአብሮ መኖር ህልውናውን አረጋግጦ ለሚቀጥለው ትውልድ ያስተላለፈውንና ያስተላለፈበትን ሁኔታ ጭምር የሚገልጽ ቅርስ ነው። ተከታዩ ትውልድ

ከቀደመው ትውልድ የተረከበውንና ራሱ ደግሞ የጨመረውን እያካተተ የሚተርክ ዘገባ ነው፡፡ (መስፍን ወልደማርያም (ፕሮፌሰር)፣ 2008)፡፡

ታሪካዊ ተውኔት አንዱ የተውኔት ዘውግ ነው፡፡ በዚህ ዘውግ ውስጥ ያሉ ብዙ ተውኔቶች እውነተኛ ታሪካዊ ሰዎችን ወይም ታሪካዊ ክስተቶችን የሚያካትቱ ታሪኮችን ይናገራሉ። ታሪካዊ ተውኔቶች ማኅበራዊ ደንቦችን፣ ባሕሎችን፣ ልማዶችንና ወጎችን ጨምሮ የወቅቱን ዝርዝሮች በተቻለ መጠን በትክክል ይይዛሉ። የግጭት፣ የባህል እና የህብረተሰብ ለውጥ ጭብጦን በማጉላት በታሪካዊ መቼቶች ውስጥ ያሉትን ውስብስብ የሰው ልጅ ልምድ ይዳስሳል (Robé Chris, 2009)፡፡

የታሪካዊ ተውኔቶች ያለፈውን እና የአሁኑን የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው። ታሪካዊ ተውኔት የተመልካቹን ሃሳብ ለመቅረጽ እንደመሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣ ይህም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ስለ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ሁነቶች ተለዋዋጭነት ግንዛቤ ይሰጣል።

ኢትዮጲያ ካላት በርካታ ታሪክ አንፃር ታሪክን ተመርኩዘው የተሰሩ የሥነጽሁፍ ስራዎች በቁጥር አነስተኛ ናቸው። ከእነዚህ ስራዎች መካከልም ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ንጉሰ ነገስት በኢትዮጲያ (አጤ ቴዎድሮስ) አንዱ ናቸው፡፡ በኪነጥበቡ ዘርፍ አጤ ቴዎድሮስ የበርካቶችን ቀልብ ገዝተው እናገኛቸዋለን፡፡ አንጋፋው ጸሃፊ (አቤ ጉበኛ፣ 1961) ትምቢታዊ በሆነ ገለጻ "ቴዎድሮስ፣ ገና ገና ወደፊት በሚመጣው የኢትዮጲያ ትውልድ ልብ ውስጥ እንደዕንቁ ያበራሉ" ብለዋል፡፡ ደራሲው ሳህለሥላሴ ከሌሎች ነገስታት በተለየ አጤ ቴዎድሮስ ለምን የኪነጥበብ ሰዎችን ቀልብ እንደሳቡ ሲገልጹ "ቴዎድሮስ የበለጠ ምቹ ናቸው፡፡ የሰውነታቸው አስደናቂ ተፈጥሮ፣ በድራማ የተሞላው ህይወታቸና ድርጊቶቻቸው ፀሃፊዎችን ይማርካል፡፡" ብለዋል (ሳህለሥላሴ ብርሃነ ማርያም፣ 1974)፡፡

ምንም እንኳን አጤ ቴዎድሮስ በደርግ ዘመነ መንግስት ገነው እንዲወጡ ተደርገዋል ቢባሉም በግርማዊ ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ስላሴ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጲያ ዘመንም በርካታ የሥነጽሁፍ ስራዎች ታሪካቸውን ተመርኩዘው ተሰርተዋል፡፡ የደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት **ቴዎድሮስ** ታሪካዊ ድራማ፣ የአቤ ጉበኛ **አንድ ለእናቱ** ልቦለድ፣ የጸጋዬ ገብረመድኅን **የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ**፣ የብርሃኑ ዘርይሁን **የቴዎድሮስ ዕንባን**

ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ በሃገር ውስጥም በውጭ ሃገር የታሪክ ጸሃፊያንም ተጽፏል፡፡ በኢትዮጲያ ታሪክ ውስጥ በርካታ ውዝግቦችን ከሚያስነሱት ታሪኮች መካከል አንዱም የአጤ ቴዎድሮስ ነው፡፡ እንደ (ጳውሎስ ኞኞ፣ 1985) አጤ ቴዎድሮስ "በመሳፍንት ተከፋፍላ የወደቀች አገራቸውን ለማንሳት የተነሱ ታላቅ አገርወዳድ መሪ ፡፡" ናቸው፡፡ (ተክለጻዲቅ መኩሪያ፣ 1928) " የቴዎድሮስ የአንድነትናየ ነጻነት ተጋድሎ፣ የመቅደላው መስዋትነት፤ በአጠቃላይ የጀግንነት አርአያነት በነጻነት ተጋዳይነት ታሪካችን ውስጥ ዘላለማዊ አንጸባራቂ ስፍራ ይዞ የሚኖር፤ የተከታታይ ትውልድ ጥልቅ አክብሮት ሊለየው የማይገባ እጅግ አኩሪ ቅርስ ነው" ይላሉ፡፡ ከውጭ ጸሃፍት እንደ (Richard Pankhurst፣1935) ቴዎድሮስ ገዥ ብቻ አልነበሩም፣ ቅኝ ገዥዎችን ወራሪዎችን እየታገሉ ኢትዮጲያን ለማዘመን የጣሩ የለውጥ አራማጅ ናቸው፡፡ Sven Rubenson፣1966 አጤ ቴዎድሮስ ባለ ራዕይ መሪ ናቸው፡፡ የኢትዮጲያን አንድነት ለማምጣት እና ኢትዮጲያን ለማዘመን የጣሩ ሃይማኖተኛ ናቸው ይላል፡፡ በሌላ በኩልም ውስብስብ፣ ጨካኝ እና አምባገነን ናቸው ይላል፡፡ ዜና መዋዕላቸውን የጻፉት (አለቃ ወልደማርያም ዘ ሸዋ፣) "የበጌ ምድር ሰው ሁሉ በቴዎድሮስ አንድ አይነት የመከራ ጽዋ በራብ፣ በእሳት፣ ተቀበለ፡፡ በየእለቱ በማናቸውም ነገር እየተያዘ የሚሞተው ሰው እንደ ልማድ ሆኖ ቁጥር የለውም፡፡" በማለት ጽፈዋል፡፡ እንደ Kofi Darkwah፣ 1969 ገለጻም ንጉሰ ነገስቱ ባህሪያቸው መልከ ብዙ ነው፡፡ ኢትዮጲያን ለማዘመን፣ አንድነቷን ለማስጠበቅ የጣሩ ባለ ራዕይ ናቸው፤ በሌላ በኩልም የሚቃወሟቸውን ሁሉ ያለ እርህራሄ በጭካኔ የሚያጠፉ ናቸው፡፡ ታሪክ እንዲህ ሁለት መልክ ሰጥቶ የሚያወሳቸውን አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጲያ ከያንያንም ብዙ ብለውላቸዋል፡፡ የጌትነት እንየው "የቴዎድሮስ ራዕይ" እና የእንዳለጌታ ከበደ "የካሣ ፈረሶች" ተውኔቶችም ከነዚህ መካከል ይገኛሉ። ሁለቱም ሥራዎች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላቸው ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን ታሪካቸውን በተለያዩ የትረካ ቴክኒኮች ያቀርባሉ። በሁለቱም ተውኔቶች ውስጥ አጼ ቴዎድሮስ የተገለጹበት መንገድ ይለያያል፡፡ ይህ ጥናት እነዚህን ተውኔቶች በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ማዕቀፍ ለመተንተን ያለመ ነው።

"የቴዎድሮስ ራዕይ" በጌትነት እንየው የተዘጋጀ ሙዚቃዊ ተውኔት ሲሆን ተውኔቱ ጥቅምት ወር ላይ 2000 ዓም ለእይታ የበቃ ነው፡፡ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና የኢትዮጲያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር ጽ/ቤት የተዘጋጀ ነው፡፡ ተውኔቱ  በዳግማዊ ቴዎድሮስ ህይወት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ወደ ስልጣን የመጡበትን መንገድ፤ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ያደረጉትን ትግልና መጨረሻቸውን የሚያሳይ ተውኔት ነው። ይህ ተውኔት ባህሪያቸውን፣ የአመራር ጥበባቸውን፣ የአንድነትና የክህደት ጭብጦችን በመዳሰስ ላይ ያተኩራል። አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የነበራቸውን ራዕይ ያንፀባርቃል፡፡ - የኢትዮጵያን ታላቅነት ለመመለስ ጥረት ሲያደርጉና በመጨረሻ አሳዛኝ ፍጻሜያቸውን ያስከተለውን ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ያስመለክታል።

‹‹የካሣፈረሶች›› በእንዳለጌታ ከበደ ነሃሴ 2009 ኢ.ም የታተመ ሲሆንያልተቀበልናቸው ከተሰኘው ወጎች፣ መጣጥፎች እና የተውኔት ድርሰት ውስጥ የተካተተ ነው፡፡ ተውኔቱ የዳግማዊ ቴዎድሮስን ትሩፋትና በዘመነ መንግሥቱ ላይ ስላሉ ታሪካዊ ክንውኖች የሚዳስሱ ተውኔቶችን እያሳየን የሳቸውን ምልከታ በተውኔት ውስጥ ባለ ተውኔት እንድናይ የሚያደርግ ነው። የሚች ኢትዮጵያውያን ሰማያዊ ጉባኤን በማቅረብ የሜታ ትያትር አካሄድን  ይከተላል። ተውኔቱየ ቴዎድሮስን ስኬቶችና ውድቀቶች እሳቸውን ተመርኩዘው በተሰሩ ተውኔቶች ላይ እያሳየ የሚተቸውን በመተቸትና የሚደነቀውን በማድነቅ ክፍተቶችን እያሳየ በኢትዮጵያ ታሪክና በጊዜው በነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ አስተያየቱን ጭምር ይሰጣል። ይህ ጥናት እነዚህን ተውኔቶች በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ማዕቀፍ ለመተንተን ያለመ ነው፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በታሪካዊ አውዶችና በጽሑፋዊ ውክልናዎች መካከል ያለውን መስተጋብር ያጎላል። ይህ ጥናት የ “ቴዎድሮስ ራዕይ” እና “የካሳ ፈረሶች” ተውኔቶችን በመመርመር እነዚህ ስራዎች ታሪካዊ ትረካዎችን እንዴት እንደሚተረጉሙ፣ ባህላዊ እሴቶችን እንዴት እንደሚያንፀባርቁ ይመረምራል። አጤ ቴዎድሮስ በተውኔቶቹ ውስጥ የተገለጹበትን መንገድ መፈተሽ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ አውዶችን ከሐዲስ ታሪካዊ ሂስ አንጻር የተገለጹበትን መንገድ ማሳየት የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አላማ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ጥናት ለማከናወን ያነሳሱኝ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ናቸው። የመጀመሪያውና ዋናው ምክንያቴ ኪነት ያገነነው አጤ የሚለውን የአብዱል ጀሊል አሊ መጸሃፍ በመመልከቴ ነው፡፡ የዚህ መፅሀፍ የተወሰነ ቦታ መገኘት እና ከቦታ ቦታ ለመፅሀፉ ያለው ምልከታ መለየት  በተለየም መፅሀፍን ለመግዛት መጸሃፍ ሻጮችን ስጠይቅ የነበረው ግልምጫና  አንዳንዶቹ እንዴት እንዲህ አይነት መጸሃፍ ይይዛሉ ብለሽ አሰብሽ ማለታቸው ለመፅሀፉ ትኩረት እንድሰጠው አደረገኝ፡፡ በንባቤም መጽሃፉ አጼ ቴዎድሮስን ኪነጥበቡ ለኛ እንደገለጸልን ሳይሆኑ አምባገነን፣ ተስፋፊ እና ጨፍጨፊ ናቸው የሚል ጭብጥን ያያዘ ነው፡፡ በተጨማሪም ፀሃፍት የንጉሰ ነገስቱን ታሪክ የነገሩበትን መንገድ የሚሞግት ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ይህ የንባብ መነሻ አጤ ቴድሮስን ኪነጥበቡ በምን መልኩ ገለፀቻቸው የሚለውን ለማጥናት እንድነሳሳ ምክንያት ሆነኝ።

ሁለተኛው ምክንያቴ ደግሞ የኢትዮጲያ ታሪክ ላይ በተለይም በአጤ ቴዎድሮስ ዙሪያ የሚነሳው ውዝግብ ሰፊ ሆኖ ሳለ በዚህ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች  በቂ አለመሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ሥነጽሁፋዊ ጥናት ውስጥ ካነሳሁት ርእሰ ጉዳይ ጋር ተቀራራቢ ሆነው ያገኜኃቸው የታየ አሰፋ፣ የሂሩት አድማሱ፣ የእጥፍወርቄ አደመ እና ነብዩ ባዩ ጥናታዊ ጽሁፎች ሲሆኑ ጥናቶቹ የጌትነት እንየው "የቴወድሮስ ራዕይ" ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡ "የካሳ ፈረሶች" ላይ የተሰሩ ጥናቶችን አግኝቶ መመርመር አልቻልኩምና የጥናቶች ውስንነት ጥናቱን ለማድረግ የበለጠ አነሳስቶኛል፡፡ ሁለቱ ተውኔቶች በዘመናችን የተጻፉ በመሆናቸው የተመረጡ ሲሆን ጥናቱን በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ የተደገፈ እና ሁለቱ ተውኔቶችን በንጽጽር ጭምር የሚያሳይ መሆኑ ካለፉት ጥናታዊ ጽሁፎች የተለየ ያደርገዋል፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በስነ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ የፈጠሩ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ከጽሁፉ ለይቶ መፈተሽ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ በሚፈጠሩ ልዩነቶችና ቅራኔዎች ላይ በመመስረት በስነጽፋዊ ውበትና ለዛ ላይ የፈጠሩትን ተፅዕኖም ይመረምራል (Tyson, 2006):: ተውኔቶቹን ከጽሁፋዊ አውዳቸው ነጥሎ ከተፈጠሩበት ዘመን ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ ጋር አዛምዶ ለማየት ስለሚረዳ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ ለጥናቱ መተንተኛነት ተመርጧል፡፡

### 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ዳግማዊ አጼ ቴዎደሮስ በ”በቴዎድሮስ ራዕይ” እና ”በካሳ ፈረሶች” ተውኔቶች ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ ፈትሾ ማሳየት ነው፡፡ ይህንን የጥናቱን ዋና ዓላማ በዝርዝር ለማየትና ለማሳካት የሚረዱ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተለት ናቸው:-

1. ተውኔቶቹ በተፈጠሩበት ዘመን የነበረው ርዕዮተ አለም በተውኔቶቹ ውስጥ ያሳደረውን ተጽዕኖ መፈተሽ፡፡
2. ተውኔቶቹ ውስጥ የሃይል ግንኙነት እንዴት እንደተቀረጸ ማብራራት፡፡
3. ዘመኑ በተውኔቶቹ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ መፈተሽ፡፡

### 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

የዚህ ጥናት ዓብይ አላማ ዳግማዊ ቴዎድሮስን "የቴዎድሮስ ራዕይ" እና "የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን አላማ ለማሳካት የሚረዱ የምርምር ጥያቄዎች ደግሞ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

1. ተውኔቶቹ የተፈጠሩበት ዘመን የነበረው ርዕዮተ አለም በተውኔቶቹ ውስጥ እንዴት ተጽዕኖ አሳረባቸው?
2. ተውኔቶቹ ውስጥ የሃይል ግንኙነት እንዴት ተቀረጸ?
3. ዘመኑ በተውኔቶቹ ላይ እንዴት ተጽዕኖ አሳደረ፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት መካሄዱ ለስነ ጽሁፍ ተማሪዎች፣ የስነ ጽሁፍ ዝንባሌ ላላቸው ሰዎች፣ በስነ ጽሁፍ ላይ ጥናት እና ምርምር ለሚያደርጉ ሰዎች ይጠቅማል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም በሁለቱ ተውኔቶች ላይ ከተደረጉ ምርምሮች በተለየ በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳባዊ ጭብጦች የተቃኘ በመሆኑ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- በአጤ ቴወድሮስ ታሪክ ዙሪያ በተለያየ የማነጻጸሪያ ንድፈ ሃሳብ ጥናት ለሚያደርጉ ምሁራን የመነሻ ሃሳብ ይሰጣል፡፡
- በጥናቱ ውጤት የተገኘውን መነሻ በመውሰድ የታሪክ ተመራማሪዎች አጤ ቴዎድሮስን በተመለከተ ጥልቅ ጥናት እንዲያስኬዱ ያነሳሳል፡፡
- አጤ ቴዎድሮስን በሐዲስ ታሪካዊ የስነጽሁፍ ንድፈ ሃሳብ አንጻር ለሚያጠኑ የዘርፉ ተመራማሪዎች መነሻ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ዳግማዊ ቴዎድሮስን "የቴዎድሮስ ራዕይ" እና "የካሳ ፈረሶች" ውስጥ ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ ማድረግ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በተውኔቶቹ ውስጥ ርዕዮተ አለም፣ የኃይል ተለዋዋጭነት እና ዘመኑ በተውኔቶቹ ላይ እንዴት ተጽዕኖ አሳደረ የሚለው ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

የጥናቱ ዘዴ ወይም ስልት እና የመረጃ አተናተን ዘዴ በዚህ ንዑስ ክፍል የተካተተ ሲሆን ተውኔቶቹ የተመረጡበት መመዘኛ፣ መረጃ ለማሰባሰብ የሚረዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የጥናቱ ዘዴ ወይም ስልት እና የመረጃ አተናተን ዘዴ የሚሉት ጉዳዮች ተካተዋል፡፡

### 1.7.1 የጥናቱ ዘዴ (ስልት)

ይህ ምርምር ሥነ ጽሁፋዊ ጥናት ከመሆኑ አኳያ መረጃዎች ተተንትነው እና ተተርጉመው የጥናቱ ውጤት የሚቀርበው በትንተና መልክ በመሆኑ ጥናት እና ምርምሩ አይነታዊ ንባብ ዘዴን የተከተለ ሲሆን የሐዲስ ታሪክ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም በተውኔቶቹ ውስጥ ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ በማድረግ በጥልቀት በመፈተሽ ጥናት እና ትንተና ይደረጋል፡፡

### 1.7.2 ተውኔቶቹ የተመረጡበት መመዘኛ

ይህ ጥናት በዋናነት ይዞት የተነሳው አብይ ጉዳይ ሥነ ጽሁፍና ታሪክ ያላቸውን ቁርኝት ከማሳየት ባለፈ በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ ጭብጦች በመመርኮዝ ተውኔቶችን መመርመር ነው፡፡ ጸሃፊ ተውኔቶችን ከማረከቸው የታሪክ ሰዎች መካከል አንዱ አጤ ቴዎድሮስ ናቸው፡፡ ታሪካቸው በውዝግብ የተሞላ እና ባለ ሁለት መልክ መሆኑ በእርሳቸው ዙሪያ የተሰሩ ስራዎች ላይ እንዳተኩር አድርጎኛል፡፡ በዚህ ምክንያትም ዳግማዊ ቴዎድሮስን በ"የቴዎድሮስ ራዕይ" እና "የካሳ ፈረሶች" ውስጥ ከሐዲስ ታሪካዊ ሂስ አንጻር እንዴት እንደተወከሉ የሚመረምር ነው፡፡ ሁለቱ ተውኔቶች በ2000 አም እና 2010 ላይ ለታዳሚ የቀረቡ ናቸው፡፡ ተውኔቶቹ በእኛ ዘመን የተፈጠሩ መሆናቸው የተፈጠሩበት ዘመን ተመሳሳይ ሆኖ እያለ ባለ ታሪኩን የቀረጹበት መንገድ የተለያየ መሆኑ የተነሳሁበትን አላማ ስለሚያሳካ እንድመርጣቸው አድርጎኛል፡፡ ሌላው ደግሞ እነዚህ ተውኔቶች በዚህ የእይታ ማእቀፍ ከዚህ ቀደም በጥናት እና ምርምር በቂ ሆነው አለመታየታቸው እና ሁለቱም ታሪካዊ ተውኔቶች በመሆናቸው በታሪክ ላይ ያለንን አረዳድ እንዲታረም እድል ይፈጥራል በሚል እሳቤ እንዲሁም የተውኔት ጽሁፎቹን የማግኜት እድል መኖሩ ተውኔቶቹን በናሙናነት ለመምረጥ የመመዘኛ መስፈርት ሆነዋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ የተመረጡ ተውኔቶች ለይቶ እና ተንትኖ ለማሳየት ያስችላል በሚል እምነት በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የተመረጡ ናቸው፡፡

### 1.7.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ጥናቱ የስነ ጽሁፋዊ ጥናት እንደ መሆኑ መጠን ቴክስት ትንተና እና አይነታዊ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ ይህ ጥናት ለትንተናው መሰረት የሚሆኑትን መረጃዎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የሚሰበስብ ሲሆን፣ እነዚህ ምንጮች ደግሞ ለዚህ ጥናት ካላቸው ቅርበት አንጻር በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተመድበዋል። በዚህም መሰረት ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለው ጥናቱ የሚካሄድባቸው "የቴዎድሮስ ራዕይ" እና "የካሳ ፈረሶች" ሲሆኑ ዳህራይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ለክለሳ ድርሳናት የሚያገለግሉ ጽሁፎች እና የጥናት ወረቀቶች፣ ልዩልዩ ድርሳናት እና መዛግብትን በመረጃ ምንጭነት ይጠቀማል፡፡ በተደጋጋሚ እና በጥልቀት በማንበብ ለጥናቱ ይበጃሉ ተብሎ የታመነባቸው መረጃዎች ሁሉ ተሰብስበዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት ውስጥ ስራ ላይ የሚውለው ምንባባዊ የትንታኔ ስልት የሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆነል ማለት ነው፡፡

### 1.7.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ "የቴዎድሮስ ራዕይ" እና "የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ወቅትም ቴክስቱን በተደጋጋሚ እና በጥልቀት በማንበብ የሚያጠነጥንባቸውን ዋና ዋና ጭብጦች (ርዕዮተ ዓለም ፣ የሃይል ተለዋዋጭነት እና በዘመኑ የነበረውን ማህበረ ፖለቲካ አውድ ) ነቅሶ በማውጣት ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ በማድረግ ተውኔቶቹ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከምርምሩ ርእሰ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት እና ዝምድና ያላቸውን የጥናት ወረቀቶች ፍተሻ እና ምርመራ ተደርገዋል፡፡ መዛግብት እና ሰነዶች ተፈትሸዋል፡፡ በፍተሻ እና ምርመራ ከተገኙት መረጃዎች ከንድፈ ሃሳብ የመተንተኛ ስልት (ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ) ጋር በማገናዘብ እና በማናበብ አደራጅቶ ግልጽ እና ተጨባጭ በሆነ መልኩ በመተንተን ለመሪ ጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

## 1.8 የምዕራፍ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ ምዕራፍ አንድ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን ምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱን ዓላማዎች፣ የጥናቱን ጠቀሜታ (ፋይዳ)፣ የጥናቱን ወሰን (ገደብ)፣ እና ውስንነቶች እንዲሁም የጥናቱን ሥነ ዘዴ አካቶ ይዘል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ደግሞ በዋናነት የጥናቱ ማዕከላዊ ጉዳይ የሚተነተንበትን የንድፈ ሃሳባዊ ጽሁፍ ክለሳ እና የቀደምት ጥናቶች ክለሳን ያካተተ ሲሆን፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ ምንነት ከነባሩ ታሪካዊ ሂስ ጋር ያለው አንድነት እና ልዩነት እንዲሁም ጭብጦቹ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ ከንድፈ ሃሳቡ ባሻገርም የቀደምት ጥናቶች ክለሳ የተካሄደባቸው ንዑስ ርዕሶች ቀርበውበታል፡፡

ምዕራፍ ሦስት ዳግማዊ ቴዎድሮስ በ"ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ"የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ፦ ሃዲስ ታሪካዊ ንባብ በሚል ርዐሰ ጉዳይ ሰባት ንዕስ ርዕሶች የተነሱ ሲሆን፣ እነዚህም፡የተውኔቶቹ አጽመ ታሪክ( የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" እና "የካሳ ፈረሶች" ታሪካዊ ተውኔቶች አጽመ ታሪክን፣ ርዕዮተ አለም በተውኔቶቹ ውስጥ እንዴት ተንጸባርቋል፣ ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ፣ የኃይል ተለዋዋጭነት፣ ዘመኑ በተውኔቶቹ ውስጥ ያሳደረው ተጽዕኖ፣ የተውኔቶቹ አንድነት እና ልዩነትን የያዘ ነው፡፡ለትንተና የተመረጡት የ "ቴዎድሮስ ራዕይ" እና "የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ላይ የተንጸባረቁት ግኝቶችንም የያዘ ነው፡፡

አራተኛ እና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ከዚህ ምዕራፍ አስቀድሞ በነበሩት ሶስት ምዕራፎች ውስጥ የተነሱት ጉዳዮች በማጠቃለያ ቀረበበት ክፍል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ

### 2.1 የንድፈ-ሃሳባዊ ጽሁፍ ክለሳ

#### 2.1.1 ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በሥነ ጽሁፍ እና በታሪክ እንዲሁም በልብወለድ እና በእውነተኛው ዓለም መካከል ልዩነት የለም የሚል እምነት አለው፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በስነ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ የፈጠሩ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን ከስነ ጽሁፋዊ ስራው ነጥሎ መመርመር ላይ ትኩረት ያደርጋል (Tyson, 2006)፡፡

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በ1970ዎቹ መጨረሻ እና በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ የተጀመረ የሂስ አይነት ነው፡፡ ስቲቨን ግሪንብላንት የሃዲስ ታሪካዊ ሂስ አባት ነው፡፡ በሱ ስራዎች ላይ ተመርኩዞ እውቅናን እያተረፈ የመጣ ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ እየጨመረ ለመጣው የስነምግባር ውድቀት ወደ ታሪክ መመለስ መፍትሂን ያመጣል በሚል እምነት ነው ንድፈ ሃሳቡ የመጣው፡፡ በታሪክ ውቅር ውስጥ በሚፈጠሩ ልዩነቶች እና ቅራኔዎች ላይ በመመስረት በስነ ጽሁፋዊ ውበት እና ለዛ ላይ የተፈጠሩትን ተፅዕኖዎችም ይመረምራል። ደራሲው ሲጽፍ የነበረበት ጊዜ እና ቦታላይ የነበሩት ሁነቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል። ደራሲው በጻፈበት ጊዜ ጽሁፉን በዚህ መንገድ እንዲጽፍ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ምክንያቶችን ይተነትናል ፡፡

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በተመሳሳይ የታሪክ ዘመን ውስጥ የተፈጠሩ ሥነ-ጽሑፋዊ እና ሥነ-ጽሑፋዊ ያልሆኑ ጽሑፎችን በትይዩ ንባብ ላይ በመመስረት የመፈተሽ ዘዴ ነው። (Barry,2009፣ 166)። በሌላ አገላለጽ ሐዲስ ታሪካዊነት ስነ-ጽሑፋዊ እና ስነ-ጽሑፋዊ ያልሆኑ ጽሑፎችን እና የተጻፉበትን ታሪካዊ ወቅት በማመሳል የመረዳት ዘዴ ነው። በጽሑፎቹ መካከል ያለው ትይዩነት፣ ሁሉም ጽሑፎች የተዛባ እና በጊዜው ተቀባይነት ካላቸው ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ልማዶች የተገኙ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ

ያስገባል። ጽሑፋዊ እና ሥነ-ጽሑፋዊ ያልሆኑ ጽሑፎችን በማጣቀስ፣ ከተመሳሳይ ታሪካዊ ጊዜ ጀምሮ አዲስ ግንዛቤን ያዳብራል።

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በስነ ጥበባዊ ስራዎች ውስጥ የቀደምት ታሪካዊ ኩነቶች በምን አይነት ጥበብ እንደተገለጹ ለመመርምር ይረዳል፡፡ በአንድ የጥበብ ስራ ውስጥ የቀደምት ታሪካዊ ሥራዎች እንዴት ተገለጹ ብሎ ለመጠየቅ እና ለመመርመር አመቺ ነው፡፡ ቀድመው የተሰሩ ጥንታዊ የጥበብ ስራዎች ታሪክን ያዩበት እና የመረመሩበት መንግድ ምን ይመስላል ብሎ ለመገምገም ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ እድል ይሰጣል (Tyson, 2006) ፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ሥነ-ምግባርን እና እምነትን በስነጽሁፍ ውስጥ ከማህበራዊ አውድ ነጥሎ ማንበብ እደሚቻል ያመላክታል። በሥነ ጽሑፍ እና በታሪክ እንዲሁም በጽሑፍ እና አውድ መካከል ያለውን ልዩነት ውድቅ ያደርጋል (Fairbrook,2015 ፣11)።

ታሪክ ማእከላዊ ነው፡- ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ታሪክ በማንኛውም ስነ-ጽሁፍ ላይ ቀጥተኛ እና የማይካድ ተፅእኖ እንዳለው አድርጎ ይመለከታል። ሁሉም ታሪካዊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡ ፅሁፉ ሲተነተን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ሁሉም መተንተን አለባቸው። እነዚህ ሁሉ ለጽሑፉ ታሪካዊ ዳራ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የሃያሲው ታሪካዊ ሁኔታዎችም ጠቃሚ ናቸው፡፡ አንድ ደራሲ በጊዜው እንደሚቀረጽ ሁሉ፣ ማንኛውም ሃያሲም ጽሑፍን ሲተነትን ያለበትን ማህበረሰብ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። ጽሁፉን በተፈጠረበት አውድ ውስጥ ማስቀመጥ፣ በታሪክ ውስጥ ያሉ ትስስሮችን መለየት፣ በትይዩ ንባብ ሥነጽሁፋዊ ስራውን ስነጽሁፋዊ ካልሆነ ጽሁፍ ጋር መመርመር አለበት፡፡

ታሪክ በጽሁፍ ይኖራል ትርጓሜዎችም ታሪክን ያድሳሉ፡፡ ታሪክ ተለዋዋጭ ነው፡፡ ማህበራዊ አወቃቀሮችን እና ባህላዊ ደንቦችን ይመረምራል፡፡ ሐዲስ ታሪክ በዋናነት ከተለያዩ የድህረ መዋቅራዊ ንድፈ ሃሳቦች በተለይም የሉዊስ አልቱዘር ማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም፣ ከሚሼል ፉኮ ኃይል በመላው ህብረተሰብ ውስጥ ይሰራጫል ከሚለው ሃሳብ ጋር የተዛመደ ነው፡፡ እውቀት ሁል ጊዜ የኃያላን ቦታን እንደሚደግፍ እና እውቀቱ በኃይል መዋቅሮች የተፈጠረ እንደሆነ ፉኮ ይናገራል፡፡ ታሪክ የሚሰራው እውቀት ባላቸው ሰዎች ነው። ኃይል ወይም ስልጣን እና አውቀት አንድ ላይ ወደ ታሪክ ይመጣሉ ( H. Aram Veeser፣ 1989)፡፡

ከነባሩ የታሪክ ሂስ ቀጥሎ የመጣው የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ እይታ መነሻው ስነ ጹሁፋዊ ስራዎች ዓለምን ትክክለኛ እና የአንድ ወጥ ነጸብራቅ አድርጎ ለሚመለከተው ማህበረሰብ ታሪክ ወጥ እና ቀጥተኛ አለመሆኑን ለማሳየት ምላሽ እንዲሆን ታስቦ የተነደፈ ነው፡፡ ሌላው የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ የእድገቱ አስፈላጊነት የዘመኑን የሥነ ጽሑፍ ሳይንስ መሪ አቀራረብ እውነታ መመርመር፣ የስነ ጽሑፋዊ ሥራውን ከባህላዊ አውድ ማውጣት እና እንደ ግለሰባዊ ጉዳይ አድርጎ በተናጠል መመልከት እንዲቻል ታስቦ ነው (Bolton, 2007) ፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በዋናነት አላማው ጽሁፍን ወደ ተፈጠረበት አውድ መመለስ ብቻ አልነበረም፡፡ ከጽሁፉ ባሻገር የታሪካዊ አውዱን ማዕከል፣ የስነጽሁፋዊ ጥናት መሰረትን እና ሌሎች በሂስ ሂደቱ ውጥ ትርጉም ያላቸውን ነባራዊ እውነቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት መመርመር ላይ ያተኩራል (Ppechter, 1987)።

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳቡ ከመምጣቱ በፊት ተስፋፍቶ የነበረውን የነባሩ ታሪካዊ ወይንም ባህላዊውን ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብ ማዕከልን መቃወሙን ያሳያል። በቀደመው ታሪካዊ ሂስ ሥነ-ጽሑፍ የተጻፈበት ታሪካዊ ጊዜ ነጸብራቅ ተደርጎ ይታይ ነበር። ነባሩ ታሪካዊ ሂስ ነባቢያዊ ሆኖ በልሂቃኑ ወይም በማህበረሰቡ ዘንድ ቅቡል በሆነ የፖለቲካ ርዕይ ላይ ትኩረት ያደርጋል (Greenblatt, 1982: 5) ፡፡

### 2.1.2 በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ እና በነባሩ ታሪካዊ ሂስ መካከል ያለው የታሪክ ግንዛቤ

በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ እና ነባሩ ሂስ በጣም የተለመዱ የንድፈ ሃሳባዊ እይታዎችን ስለሚጋሩ ለሥነጽሁፋዊ ትርጉም ያላቸው አቀራረብ ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ ነው፡፡ ልዩነቶችን በግልጽ ለማየት ሁለቱን ዘርፎች ለይቶ ለየብቻቸው ለማየት ያስፈልጋል (Montrose, 1989) ፡፡

በ1944 በአሜሪካዊ የታሪክ ጸሐፊ የተፃፈውን የአብዮታዊ ጦርነት ውጊያ ዘገባን ለአብነት ብንወስድ እና በነባሩ ታሪካዊ ሂስ ብንመለከተው በአብዛኛው ስለታሪክ የሚጠይቀው ጥያቄ “ይህ ትክክል ነው?” ወይም “ይህ ውጊያ ስለተደረገበት‘ የዘመን መንፈስ ’ምን ይነግረናል? ” የሚል ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ይህንን የጦርነት ታሪክ የሚያነብ የሐዲስ ታሪክ ሃያሲ ሊያነሳው የሚችለው ጥያቄ “ስለ 1944ቱ አብዮታዊ ጦርነት የፖለቲካ አጀንዳዎች እና ርዕዮተ ዓለማዊ ግጭቶች ይህ ዘገባ ምን ይነግረናል?” የሚል ይሆናል፡፡ ጦርነቱን

በሚመለከት የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ፍላጎት እና ጥያቄ የወቅቱን ትግል፣ ውጊያው የተወከለበትን መንገድ (በጋዜጣ፣ በመጽሄት፣ ትርክት፣ መንግስታዊ ዶክመንቶች፣ ታሪክ፣ ንግግር፣ ስዕል እና ፎቶግራፍ)፣ በአሜሪካዊ ቅኝ ገዥዎች ወይስ በምዕራባዊያ፣ እነዚህ ውክልናዎች የአሜሪካ አብዮት በወከሏቸው ባህሎች እንዴት እንደተቀረጸ እና ምን እንደቀየረ ይነግሩናል? " የሚል ይሆናል (Tyson, 2006፣282) ፡፡

ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ትላለች ታይሰን "በታሪክ እና ታሪክን የምንመረምርበት ሂደት መካከል በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ እና በነባሩ ታሪካዊ ሂስ መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ለይቶ ያሳየናል" (Tyson, 2006 ፣282)፡፡ በነባሩ (ባህላዊው) ታሪካዊ ሂስ መሰረት "ምን እንደተፈጠረ" እና "የተፈጠረው ነገር ስለ ታሪኩ ምን ይነግረናል" በሚል ሃሳባዊ ሃሰሳ ላይ ተመስርቷል፡፡ በአንፃሩ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ የሚመረመረው "ሁነቱ እንዴት ተወከለ" እና "የሁነቱ ትርጉም ስለተርጓሚዎቹ ምን ይነግረናል" በሚሉ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በነባሩ ታሪካዊ ሂስ እይታ ታሪክ የነገሮች ቀጥተኛ ምክንያት እና ውጤት ስሪት አድርጎ መመልከት ይስተዋል ነበር፡፡ በተጨማሪም ሰዎች ምክንያታዊ ሆነው ያልተመረመሩ እና ያልተደረሰባቸውን ታሪካዊ ሁነቶችን የመመርመር አቅም አላቸው ብለው ያምናሉ፡፡ ነገር ግን በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ይህ የነባሩ ታሪካዊ ሂስ የምርምር መንገድ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ሁሉንም ያለፈ ዘመን ታሪካዊ ሁነት ለመመርመር የሚያስችል እርሾ አለ ብለው ያምናሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ፍንጭ ሊሰጥ እንጂ ሙሉ በሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚገባ የመረጃ ምንጭ በታሪካዊ ሁነት ውስጥ አይኖርም ባይ ናቸው፡፡ እንደ ታይሰን እይታ የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ተከታዮች ዋናው እና ጠቃሚው እይታ ታሪካዊ ምርምር እንደግለሰቦች እይታ ይወሰናል እንጂ ወጥ እና አንድ አይነት አይሆንም የሚለው ነው፡፡ "የታሪክ ተመራማሪዎች ታሪክን የሚመረምሩበት መንገድ ወጥ እና አንድ አይነት እንደሆነ ሊያምኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ትክክል እና ስህተት፣ ስልጡን እና ኋላ ቀር፣ ጠቃሚ እና ጎጅ እና መሰል መስፈርቶቻቸው ሁነቶችን እንደሚተረጉሙበት መንገድ ልዩነት ይኖረዋል" (Tyson, 2006 ፣283)፡፡

ታሪክ ቀጥተኛ የሆነ ምክንያታዊ ግንኙነት ያላቸው ተከታታይ ክስተቶች ውጤት ነው፡፡ በሁነቶች ቀጥተኛ ትንተና የታሪካዊ ክስተቶችን እውነት የማውጣት ፍጹማዊ ችሎታ

እንዳሏቸው አድርገው ያምናሉ፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ሁለንም ያለፈ ዘመን  ታሪካዊ ሁነት ለመመርመር  የሚያስችል እርሾ አለ ብለው ያምናሉ፡፡ በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ፍንጭ ሊሰጥ እንጂ ሙሉ በሙለ እምነት ሊጣልበት የሚገባ የመረጃ ምንጭ በታሪካዊ ሁነት ውስጥ አይኖርም ባይ ናቸው፡፡ ባህላዊ (ነባሩ) የታሪክ ሃያሲያን ታሪክን የመጀመሪያ ደረጃ እና ሥነ ጽሑፍ ሁለተኛ ደረጃ አድርገው ይመለከቱታል። ሐዲስ ታሪካዊ ሃያሲዎች ጽሑፎችን ብቻቸውን ማጥናት እንደማይችሉ ያምናሉ። ትኩረቱ ከፅሁፉ ውጭ ያሉ ነገሮችን መመልከት ነው። ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በሥነ ጽሁፍ እና በታሪክ እንዲሁም በልብወለድ እና በእውነተኛው ዓለም መካከል ልዩነት የለም የሚል እምነት አለው፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በስነ ጽሁፋዊ ስራዎች ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ የፈጠሩ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን ከስነ ጽሁፋዊ ስራው አውጥቶ መመርመር ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በታሪክ ውቅር ውስጥ በሚፈጠሩ ልዩነቶች እና ቅራኔዎች ላይ በመመስረት በስነ ጽሁፊዊ ውበት እና ለዛ ላይ የፈጠሩትን ተፅዕኖም ይመረምራል። ደራሲው ሲጽፍ የነበረበት ጊዜ እና ቦታላይ ከነበሩትን ሁነቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል።ደራሲው በጻፉት ጊዜ ጽሁፉን በዚህ መንገድ እንዲጽፍ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ምክንያቶችን ይተነትናል ፡፡

በአንጻሩ፣ ሐዲስ ታሪካዊ ታሪክን በጥርጣሬ ይመለከታል (ታሪካዊ ትረካ በባህሪው ተገዥ ነው)፣ ግን ደግሞ በሰፊው; ታሪክ በማንኛውም እድሜ ውስጥ በስራ ላይ ያሉትን ሁሉንም ባህላዊ፣ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ፣አንትሮፖሎጂካል ንግግሮች ያካትታል።ስለሆነም እነዚህ የተለያዩ "ፅሁፎች" በማንኛውም ጊዜ በሥራ ላይ ያሉ ብዙ ንግግሮች ደራሲውን እና ጽሑፉን ይነካሉ። ሁለቱም የማይታለፉ የማህበራዊ ግንባታ አካል ናቸው።

በአብዛኛው በነባሩ ሂስ እይታ ታሪክ የነገሮች ምክንያት እና ውጤት ስሪት አድርጎ መመልከት ይስተዋላል፡፡ በተጨማሪም ሰዎች ምክንያታዊ ሆነው ያልተመረመሩ እና ያልተደረሰባቸው  ታሪካዊ ሁነቶችን የመመርመር አቅም አላቸው ብለው ያምናሉ፡፡ እንደውም አንዳንዶቹ የአንድን ማህበረሰብ ስሪት ዘላለማዊ መሰረቶች ተደርገው ይወሰዱ ነበር፡፡ ነገር ግን በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ይህ የነባሩ ታሪካዊ ሂስ የምርምር መንገድ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ሁሉንም ያለፈውን ዘመን ታሪካዊ ሁነት ለመመርመር የሚያስችል እርሾ አለ ብለው ያምናሉ፡፤

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ፍንጭ ሊሰጥ እንጂ ሙሉ በሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚገባ የመረጃ ምንጭ በታሪካዊ ሁነት ውስጥ አይኖርም ባይ ናቸው፡፡ እንደ ታይሰን እይታ የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ተከታዮች ዋናው እና ጠቃሚው እታ ታሪካዊ ምርምር እንደግለሰቦች እይታ ይወሰናል እንጂ ወጥ እና አንድ አይነት አይሆንም የሚለው ነው፡፡ "የታሪክ ተመራማሪዎች ታሪክን የሚመረመሩበት መንገድ ወጥ እና አንድአይነት እንደሆነ ሊያምኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ትክክል እና ስህተት፤ ስልጡን እና ኃላ ቀር፤ ጠቃሚ፣ ጎጂ እና መሰል መስፈርቶቻቸው ሁነቶችን እንደሚተረጉሙበት መንገድ ልዩነት ይኖረዋል" (Tyson፣2006፣283)፡፡

ታሪክ ተሰንዶ የሚገኘው ከሰነዶች፣ ከህግ መዛግብት፣ ከደብዳቤዎች፣ ከማስታወሻ ደብተሮች፣ ከንግግሮች እና ከአንድ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ በተፈጠሩ ሁነቶች በአካል ተገኝተው በተከተቡ መረጃዎች አማካንነት ነው፡፡ እነዚህ መሰል የታሪክ ሰነዶች ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች ሲሆኑ የዘመኑን መንፈስ እና ስልጣኔ፣አስተሳሰብ እና ሞራል፣ እሳቤ እና ርዕዮተ አለማዊ አስተሳሰቦች ታሳቢ ያደረገ ጥልቅ ጥንታኔ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በታሪክ አጥኚዎች የተመዘገቡ የታሪክ ሰነዶች ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ነገር ግን ትታኔ የሚሰራባቸው መንገድ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች በሚመረመሩበት አግባብ እና ሂደት መሰረት ይሆናል፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ሁለቱም የመረጃ ምንጮች ታሪክን ለመመርመር እና ትንታኔ ለመስጠት ጠቀሜታቸው እኩል እና ተመሳሳይ እንደሆነ ግምት ውስጥ ያስገባል (Tyson፣2006)፡፡

ጋላገር ስለ ሐዲሱ ታሪካዊነት በሰፊው ጽፋለች፣ The New Historicism (1989፣ 68)

> ስነ-ጽሁፍ ከተመረተባቸው ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ባህላዊ አውዶች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ የስነ-ፅሁፍ ሂሳዊ ትንተና የደራሲያንን ታሪካዊ እና ባህላዊ ዳራ እና ስራዎቻቸውን ትኩረት መስጠት አለበት። ሁሉም ጽሑፎች በተፈጠሩበት ጊዜ በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ስለ አንድ ጽሁፍ በቅርበት በመተንተን አንድ አንባቢ ስራው በተጻፈበት ጊዜ የነበረውን እምነት እና አመለካከት ግንዛቤ ማግኘት ይችላል።

### 2.1.3 የሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ጭብጦች

#### 2.1.3.1 ርዕዮተ አለም

ርዕዮተ አለም (Ideology) የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በማህበራዊ ሳይንስ መዝገበ ቃላት የሰፈረው በ18ተኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ገደማ ኮንት ትሬሲ በተባለ ሊቅ አማካኝነት ነው፡፡ ትርጓሜውም ጽንሰ ሃሳቦችን የሚያጠና ሳይንስ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ትርጓሜው እምብዛም አይታወቅም፤ ከዚህ ይልቅ ርዕዮተ አለም የጥናት መስክ ሳይሆን የተለያዩ ተያያዥነት ያላቸው ሃሳቦችን ሃሳቦቹ ስለሚወልዱት ወይም ስለሚያመላክቱት ጉዳዮች የሚገልጽ አንድ ቃል ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

ርዕዮተ ዓለም የሚያመለክተው ስለ ዓለም፣ ስለሃገራት፣ ስለ ማህበረሰብ ግለሰባዊ እና የጋራ ግንዛቤን የሚቀርፁ የእምነት እሴቶች እና የሃሳቦች ስብስብ ነው። በሥነ ጽሑፍ ውስጥ፣ ርዕዮተ ዓለም ትረካዎችን፣ የገጸ-ባሕሪያትን እድገት እና ጭብጦችን በመቅረጽ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ሥነ-ጽሑፍ በጊዜው የነበረውን ርዕዮተ ዓለም የሚያንፀባርቅ፣ የሚተች ወይንም የሚገነባ በመሆኑ በርዕዮተ ዓለም እና ሥነ ጽሑፍ መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብ ነው።

ስነ-ጽሁፍ ብዙውን ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና አስተሳሰቦች ያንጸባርቃል። ደራሲያን በሥራቸው ላይ ያሉትን ማህበራዊ ደንቦችን፣ የፖለቲካ እምነቶችን እና ባህላዊ እሴቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ፣ ይህም ስለ ታሪካዊው ሁኔታ ግንዛቤን ይሰጣል። በሥነ ጽሑፍ ንድፈ-ሐሳብ፣ በተለይም ከሐዲስ የታሪክ አመለካከት አንፃር፣ ርዕዮተ ዓለም የሚያመለክተው የእምነት፣ የእሴቶች እና የአስተሳሰብ ማዕከሎችን ነው። ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች በዙሪያቸው ያለውን ዓለም የሚረዱበትን እና የሚተረጉሙት መንገድ ይመለከታል።

ርዕዮተ ዓለም ሃይል እንዴት እንደሚከፋፈል ወይንም እንደሚሰራጭ፣ ማህበራዊ ደንቦች እንዴት እንደሚመሰረቱ እና ግለሰቦች በባህላዊ አውድ ውስጥ እንዴት እንደሚገናኙ ምን ተጽእኖ እንዳደረገባቸው የሚመረምር ነው። ብዙውን ጊዜ በስልጣን ላይ ያሉትን ሰዎች ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ህብረተሰብን የሚያስተዳድሩትን ዋና ዋና ታሪኮችን እና አካሄዶችን ያጠቃልላል። ከማርክሲስት ቲዎሪ በተለየ መልኩ ርዕዮተ ዓለምን ለመቆጣጠር የገዢው

መደብ መሳሪያ አድርጎ ይቀርጻል፣ ሐዲስ ታሪክም እንደ ሚሼል ፉኮ ያሉ ሊቃውንቱ እንደሚሉት የሀይል ግንኙነት መረብን በማጉላት ማህበራዊ ተዋረዶችን ተፈጥሯዊ የሚያደርግ ነው በማለት ነው (Greenblatt፣1980)፡፡

በሥነ-ጽሑፋዊ ጥናቶች ውስጥ ርዕዮተ ዓለም የሚያመለክተው ጽሑፎች ኃይልን፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን እና ባህላዊ ደንቦችን እንዴት እንደሚወክሉ የሚቀርጹትን የእምነት፣ እሴቶች እና የአመለካከት ሥርዓቶች ነው። በሐዲስ የታሪክ ሊቃውንት እይታ ርዕዮተ ዓለም የሃሳብ ስብስብ ብቻ ሳይሆን በታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ የተካተተ፣ በሥነ ጽሑፍ ውስጥም በመቅረጽም ሆነ የተቀረጸውን በመቀበል ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ነው። በአልቱዘር ማዕቀፍ ውስጥ ያለው ኃይል የሚሠራው በአካላዊ ማስገደድ ብቻ ሳይሆን በርዕዮተ ዓለም ቁጥጥርም ጭምር ነው። ርዕዮተ ዓለም፣ በአልቱዘር አመለካከት፣ ያሉትን የኃይል ግንኙነቶች የሚደግፉ የእምነት ሥርዓቶችን በመፍጠር እና በማስቀጠል ያለውን ሁኔታ ለማስቀጠል ያገለግላል። ይህም የኃይል አወቃቀሮችን ለመጠበቅ እንዲተባበሩ ያደርጋቸዋል (Althusser፣1970)፡፡

#### 2.1.3.1.2 የርዕዮተ አለም ቁልፍ ገጽታዎች፡-

ርዕዮተ ዓለሞች የሰዎችን የነባራዊ ሁኔታ ግንዛቤ የሚያሳውቁ ከተለያዩ እምነቶች የተዋቀሩ ናቸው። እነዚህም የፖለቲካ አስተሳሰቦችን (እንደ ሊበራሊዝም ወይም ወግ አጥባቂነት)፣ ሃይማኖታዊ እምነቶች፣ ኢኮኖሚያዊ ንድፈ ሐሳቦች እና ባህላዊ ደንቦች ሊያካትቱ ይችላሉ።

ርዕዮተ ዓለም ከኃይል ጋር በቅርበት የተሳሰረ ነው። ብዙውን ጊዜ የገዢ ቡድኖችን ጥቅም በማስጠበቅ ሌሎችን እያገለለ ያለውን ሁኔታ ለማስረዳት እና ለማስጠበቅ ያገለግላሉ። ርዕዮተ ዓለምን መረዳት ከተወሰኑ ማህበራዊ አወቃቀሮች እና ትረካዎች ማን እንደሚጠቀም ለማወቅ ይረዳል። ርዕዮተ ዓለም እንዴት በኃይል መዋቅሮች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ሥነ-ጽሑፍ ሊገልጽ ይችላል። በገጸ-ባህሪያት ደራሲዎች የጭቆና፣ የተቃውሞ እና የማህበራዊ ፍትህ ጭብጦችን ይመረምራሉ፡፡

ርዕዮተ ዓለሞች ቋሚ አይደሉም። በጊዜ ሂደት ይሻሻላሉ። ሊሞገቱም ይችላሉ። እነዚህ እሳቤዎች የተገነቡት በባህላዊ ልምዶች፣ በስነ-ጽሑፍ፣ በስነ-ጥበባት እና ንግግር ነው። ይህም የሰውን ልጅ ልምድ ውስብስብነት በማንፀባረቅ ነው። ስነ ጽሑፍ የበላይ የሆኑትን አስተሳሰቦች ሊያጠናክር ቢችልም፣ ለመተቸት እና ለመቃወም መድረክ ሆኖ ያገለግላል።

### 2.1.3.1.3 ርዕዮተ አለም በስነጽሁፍ ሲተገበር

ጽሑፎች በጊዜያቸው የርዕዮተ ዓለም ማዕቀፎች ውጤቶች ሲሆኑ በማኅበረሰቡ እምነት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የርዕዮተ ዓለም ጥናት ትረካዎች እንዴት እንደተገነቡ እና ከህብረተሰቡ እምነት ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ለመረዳት አስፈላጊ ነው። የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን በርዕዮተ ዓለም መነጽር በመመርመር፣ ተመራማሪዎች የሥልጣን፣ የውክልና እና የተቃውሞ ውስብስብ አካሄዶችን በባህላዊ አውድ ውስጥ ማወቅ ይችላሉ፣ ይህም በሥነ ጽሑፍ እና ርዕዮተ ዓለም መካከል ያለውን ተለዋዋጭ ግንኙነት ያሳያል።

ርዕዮተ ዓለም በሐዲስ ታሪክ አውድ ውስጥ የሚያመለክተው ማኅበራዊ አወቃቀሮችን እና ባህላዊ ልማዶችን የሚያስታውቁ የእምነት ሥርዓቶችን ነው። በዚህ መነፅር ስነ-ጽሁፍን መተንተን ፅሁፎች እንዴት ከዘመናቸው ርዕዮተ አለም ጋር እንደሚገናኙ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖር ያስችላል፣ ይህም በሁለቱም ታሪካዊ ሁኔታዎች እና ወቅታዊ ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤዎችን ያሳያል።

የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ከታሪካዊ ጊዜያቸው የማይነጣጠሉ ናቸው። ሐዲስ የታሪክ ሊቃውንት ጽሑፎች እንዴት ከወቅታዊ ርዕዮተ ዓለም ጋር እንደሚገናኙ ይመረምራሉ። "ተጨባጭ" ታሪክ ወይም ርዕዮተ ዓለም የለም; ሁሉም ትረካዎች በዘመናቸው አድሏዊነት የተቀረጹ ናቸው ይላል ሐዲስ ታሪካዊነት። ስነ-ጽሁፍ ይህንን ማዕቀፍ የሚያንፀባርቅ ብቻ ሳይሆን በግንባታው፣ በውድድርነቱ እና በዝግመተ ለውጥ ውስጥ በንቃት ይሳተፋል። ሐዲስ የታሪክ ሊቃውንት ጽሑፎችን በታሪካዊ አውድ ውስጥ በማስቀመጥ ርዕዮተ ዓለም የሁለቱም ውጤት እና የሰውን አገላለጽ የሚቀርጽ ኃይል እንዴት እንደሆነ ይገነዘባሉ።

ርዕዮተ አለምን ከሐዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሃሳብ አንጻር በጽሁፍ ውስጥ ስንተገብር ለምሳሌ፡- የአልቱሰርን ንድፈ ሐሳብ ወስደን ጽሁፉ ላይ ስንተገብር፣ ጽሁፉ በዘመኑ ከነበሩት ዋና ዋና

አስተሳሰቦች ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ወይም ዘመኑን እንደሚተች ልንመረምርበት እንችላለን፡፡

ሀ. ርዕዮተ ዓለምን ማጠናከር

ተውኔቶች ብዙውን ጊዜ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ገፀ-ባህሪያትን እና ሁኔታዎችን ከሃገሪቱ እምነት እና እሴቶች ጋር የሚጣጣሙ ርዕዮተ ዓለምን ለማጠናከር ያገለግላሉ። ለምሳሌ፣ ቲያትር የንጉሳዊ አገዛዝን ህጋዊነት ወይም ማህበራዊ ተዋረድን የማስጠበቅ አስፈላጊነት ያሳያል፣ በዚህም የፖለቲካ ስርአት እና ቁጥጥር ርዕዮተ አለምን ያጠናክራል።

ለ. ርዕዮተ ዓለምን ማፍረስ ወይም መተቸት።

በአማራጭ በተውኔቱ ውስጥ የበላይ የሆኑትን አስተሳሰቦች በመገልበጥ ወይም በመተቸት፣ ያለውን ሁኔታ በመቃወም እና ባለው ስርዓት ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች ወይም ኢፍትሃዊ ድርጊቶች በማጋለጥ ነው። ለምሳሌ፣ ገፀ-ባህሪያት የፖለቲካ ስርአቶችን ህጋዊነት ሊጠራጠሩ፣ የስርዓተ-ፆታ ደንቦችን ሊቃወሙ ወይም ማህበራዊ ተዋረዶችን ሊቃወሙ ይችላሉ። ከዚህ አንፃር ተውኔቱ የርዕዮተ ዓለም እንደ መሣሪያ የሚጠቀም ይሆናል።

ገፀ-ባህሪያት በጊዜያቸው ርዕዮተ-ዓለሞች ሲቀረፁ፣ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ እነዚህን አስተሳሰቦች ወደ ውስጥ አስገብተው ወይም ሲቃወሙና ሲሞግቱ ይታያሉ። ርዕዮተ ዓለሞች ሰዎችን ለመቆጣጠር እና ለማንበርከክ የሚጠቀሙባቸውን መንገዶች ያሳያል።

ፈረንሳዊው ፈላስፋ ሉዊስ አልቱሰር በሴሚናል ድርሰቱ “Ideology and Ideological State Apparatuses” (1970) ጽንሰ ሃሳቦቹን በማስተዋወቅ መንግስታት ስልጣናቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ እና የካፒታሊዝም ማህበራዊ ግንኙነቶችን እንዴት እንደሚቀርጹ ያስረዳል። እንደ Althusser፣1970

1. አፋኝ ግዛት መሳሪያዎች (RSAs)

አፋኝ የመንግስት አካላት በህብረተሰቡ ውስጥ ስርዓትን እና ቁጥጥርን ለማስጠበቅ በሃይል ወይም በአመጽ የሚሰሩ ተቋማት ናቸው። እነሱም ፖሊስ፣ ወታደራዊ፣ የሕግ ሥርዓት እና እስር ቤቶችን ያጠቃልላሉ። RSAዎች የሚታዩ እና ቀጥተኛ የስልጣን መንገዶች ናቸው፣

ሰዎች ህጎችን እና መመሪያዎችን እንዲያከብሩ እና የተቋቋመውን ስርዓት የሚቃወሙትን የሚቀጣ። ብዙ ጊዜ በገጸ-ባህሪያት ወይም ስልጣንን፣ ህግ እና ስርዓትን በሚወክሉ ተቋማት ተመስለዋል። እነዚህ አኃዞች ወይም አወቃቀሮች ኃይልን የሚቆጣጠሩት በግዳጅ፣ በፍርሃት ወይም በቅጣት ነው። የመንግስት ስልጣንን የሚወክሉ ገፀ-ባህሪያት ጥቃትን ወይም ዛቻን በመጠቀም ቁጥጥርን በቀጥታ ሊያስፈጽሙ ይችላሉ። በጉልበት ወይም በማስፈራራት ያለውን ሁኔታ የሚደግፉ የህግ ስርዓቶች፣ፖሊስ ወይም ወታደራዊ ሰዎች መኖራቸውም እሙን ነው።

## 2 ርዕዮተ ዓለም በስነጽሁፍ ውስጥ ማስፈጸሚያ መንገድ

ርዕዮተ ዓለም (Ideological State Apparatuses) የሚሠሩት በርዕዮተ ዓለም አማካይነት ነው፣ ነባሩን ሁኔታ የሚጠብቀው በቀጥታ በኃይል ሳይሆን በአስተሳሰቦች፣ በእምነቶች፣ በእሴቶች እና በባህላዊ ደንቦች ነው። እነዚህም እንደ ትምህርት ቤቶች፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ ቤተሰብ፣ ሚዲያ እና የባህል ተቋማት ያሉ ተቋማትን ያካትታሉ። ISA የግለሰቦችን እምነት ለመቅረጽ ይረዳል ይህም አውራ ርዕዮተ ዓለምን ተፈጥሯዊ ወይም የማያጠራጥር አድርጎ በማቅረብ በራሳቸው መገዛት ውስጥ ተባባሪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ISA ብዙውን ጊዜ በባህላዊ ወይም በማህበራዊ ተቋማት፣ ርዕዮተ ዓለምን በሚያራምዱ ገፀ-ባህሪያት፣ ወይም የህብረተሰብ ደንቦች ግለሰቦች እንዴት እንደሚያስቡ፣ እንደሚሰሩ እና ያለውን ስርዓት እንደሚቀበሉ ወይም እንደማይቀበሉ ተጽእኗቸውን ያሳያሉ። ገፀ-ባህሪያት አንዳንድ አስተሳሰቦችን በሚያንፀባርቁ ወይም በሚያስፈጽም መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ።

### ርዕዮተ ዓለም በስነ ጽሁፍ

ስነ-ጽሁፍ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚታየው የርዕዮተ ዓለም ሞገድ ጋር በጥልቅ የተሳሰረ፣ በጊዜው የተፈጠረ ውጤት ተደርጎ ይወሰዳል። ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ በተለያዩ ፅሁፎች እና በዐውደ-ጽሑፉ መካከል ያለውን ግንኙነት ትኩረት ይሰጣል፣ የተለያዩ ስነጽሁፋዊ ስራዎች እንዴት ከዋና አስተሳሰቦች ጋር እንደሚገናኙ ወይም እንደሚቃወሙ ይመረምራል።

• **መገንባት እና ማፍረስ፡-** ስነ-ጽሁፍ የበላይ የሆኑ አስተሳሰቦችን ሊያጠናክር ቢችልም የተቃውሞ መንገድ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ሐዲስ የታሪክ ሊቃውንት ደራሲዎች የተስፋፋውን እምነት እንዴት መቃወም ወይም አማራጭ አመለካከቶችን በትረካዎቻቸው

ሊያቀርቡ እንደሚችሉ ይመረምራሉ። ስነ ጽሑፍ የበላይ የሆኑትን አስተሳሰቦች ሊያጠናክር ቢችልም፣ ለመተቸት እና ለመቃወም መድረክ ሆኖ ያገለግላል። ደራሲዎች የህብረተሰቡን ደንቦች መቃወም እና አማራጭ አመለካከቶችን ሊያቀርቡ ይችላሉ፣ ይህም አንባቢዎች የተመሰረቱ እምነቶችን እንዲጠይቁ ይገፋፋቸዋል።

በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ማፍረስ ብዙውን ጊዜ ስልጣንን በመጠየቅ፣ በመተቸት ወይም በመሳለቅ፣ ኢፍትሃዊነትን በማጉላት እና በስልጣን፣ በፆታ፣ በዘር፣ በመደብ ወይም በሞራል ላይ አማራጭ አመለካከቶችን ያቀርባል። በግሪንብላት ማዕቀፍ ውስጥ፣ ማፍረስ ብዙውን ጊዜ በሥነ-ጽሑፋዊ ጽሑፎች ውስጥ ኮድ ወይም ስውር ነው። ተውኔቱ የተወሰኑ እሴቶችን ወይም ርዕዮተ ዓለሞችን የሚደግፍ ቢመስልም ብዙውን ጊዜ እነዚህን እምነቶች የሚቃወሙ ወይም የሚተቹ ስውር አካላትን ሊይዝ ይችላል፤ ብዙውን ጊዜ በግልጽ አደገኛ ወይም በጊዜው ለነበሩ ባለሥልጣናት አብዮታዊ ባልሆኑ መንገዶች የሚገልጽ ነው። ይህ ጽሁፉ ከዘውግ ወይም ከማህበራዊ ሁኔታ የሚጠበቁትን አሁንም እየጠበቀ በተቃውሞ ውስጥ እንዲሳተፍ ያስችለዋል።

### 2.1.3.2 የሃይል ግንኙነት

ሐዲስ የታሪክ ሊቃውንት በሥነ ጽሑፍ እና በታሪክ መካከል ያለውን ግንኙነት እርስ በእርሱ የተቆራኘ አንዱ ሌላው ላይ ተጽእኖን የሚያሳድር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ስነ-ጽሁፍ የታሪክ ነጸብራቅ ብቻ ሳይሆን ታሪክን የሚቀረጽ እና የሚቀረጽውም በታሪካዊ ሃይሎች ነው ይላሉ። ይህንን ከሚቀርጹ መንገዶች አንዱ ሃይል ግንኙነት ነው፡፡ የሃይል ግንኙነት ከሃዲስ ታሪካዊ ሂስ ስነጽሁፋዊ ንድፈ ሃሳቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የሐዲስ የታሪክ ሊቃውንት የሆነው ሚሸል ፉኮ ስለ ሃይል ግንኙነት የነደፋቸው ንድፈ ሃሳቦችም በምሁራን፤ በህብረተሰቡ፣ እና በስልጣን ባለቤቶች ውስጥ ያለውን የሃይል ተለዋዋጭነት የሚያሳይ ነው። ስነ-ጽሁፍ የተፈጠረው በባዶ ነገር ላይ ሳይሆን በጊዜው ከነበረው ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ተለዋዋጭነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። (Foucault,1980)፡፡

የፉኮ ሁለቱ ስራዎች የሃይል፣ የንግግር እና የእውቀት ፅንሰ-ሀሳቦች ለሃዲስ ታሪካዊነት እድገት ማዕከላዊ ነበሩ። ኃይል በቋንቋ እና በተቋማት በሚሠራበት መንገድ ላይ የሰጠው ትኩረት በስነ ጽሑፍ እና በታሪክ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመተንተን ማዕቀፍ

አዘጋጅቷል፡፡ የፉኮ የ "ንግግር" ጽንሰ-ሐሳብ የእውቀት እና የኃይል ግንኙነቶች ስርዓትን በተለይም ሃዲስ የታሪክ ተመራማሪዎችን አስተሳሰብ በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ሚና ነበረው፡፡

ሃይል ቀጣይነት ያለው ዕውቀት፣ ዕውቀትም ቀጣይነት ያለው ሃይል ነው ይላል ፉኮ፡፡ እሳቤዎች በመንግስት ተቋማት ወይም የበላይ አካላት ብቻ የተያዙ ሳይሆኑ ኃይል በተፈጥሮው ያልተማከለ፣ የተንሰራፋ ብቻ ሳይሆን ከታች ሆኖ የሚሰራ እና በሁሉም የማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ የሚሰራጭ ነው (Foucault, 1978: 94)፡፡

ታሪክ እና እውቀት የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ታሪክ የሚሰራው እውቀት ባላቸው ሰዎች ነው፡፡ ሃይል ስልጣን እና አውቀት አንድላይ ታሪክ ይፈጥራሉ፡፡ በሃይል እና በእውቀት መካከል ያለው የማይነጣጠል ግንኙነት ስነ-ጽሑፋዊ ፅሁፎች እንዴት እንደሚቀርጽ፣ ኃይል በሁሉም የባህል ዘርፎች እንዴት እንደሚሽከረከር መመርመር የሚያስችል ነው ሃዲስ ታሪካዊ ሂስ፡፡

እንደ ፉኮ የሃይል ፅንሰ-ሀሳብ ተለዋዋጭነት እንደ ንጉሣዊ ፍርድ ቤቶች ወይም የሕግ አውጭ አካላት ባሉ ቦታዎች ላይ ብቻ ሳይሆን ተራ በሚመስሉ የባህል ቦታዎች ጭምር ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የሕክምና ጽሑፎች፣ የሥርዓት መመሪያዎች፣ የጉዞ ትረካዎች እና ሌሎች ሥነ ጽሑፍ ያልሆኑ ጽሑፎች ከሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ጋር አብረው ይሰራጫሉ።

ስነ-ጽሁፍ ስራዎች የታሪካዊ ሁኔታዎች ነጸብራቆች ብቻ ሳይሆኑ የማህበራዊ ሃይል የሚዘዋወርበት እና የሚቀየርባቸው የድርድር እና የመለዋወጫ ስፍራዎች ናቸው። ይህ የተገላቢጦሽ ሞዴል የኃይል ግንኙነቶችን በመገንባት፣ በማጠናከር እና አንዳንዴም በማፍረስ ላይ ስነ-ጽሑፋዊ ጽሑፎች ይሳተፋሉ። (Veeser, H.1994)

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ስነ-ጽሁፍ አሁን ያሉትን የሃይል አወቃቀሮች እንዴት እንደሚያጠናክር ወይም እንደሚገለባበጥ እና ለእውቀትና ርዕዮተ አለም ስርጭት እንዴት አስተዋፅኦ እንዳለው ይመረምራል፡፡ ሐዲስ ታሪካዊነት በመሠረታዊ መልኩ በሥነ ጽሑፍ፣ በታሪካዊ አውድ፣ እና በኃይል ግንኙነቶች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት መረዳት እንዳለብን መሰረት ጥሏል፡፡

ታሪክ የማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን የስነጽሁፍም ተመጋጋቢ ውጤት ነው፡፡ የስነ ጽሁፍ ስራዎች በተፈጠሩበት ዘመን ያለው ማህበራዊ ፖለቲካዊ አውድ ነጸብራቆች ናቸው፡፡ (pietruszynski, 2006)፡፡

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ

በዚህ የምርምር ክፍል ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ እና ቅርበት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ደሰሳ እና ምልከታ ተደርጎባቸዋል፡፡ አጥኝዋ ጥናቷ ጋር ተያያዥ የሆኑ ቀደምት ጥናቶችን የምልከታ ስታደርግ ያገኟቻቸው ጥናቶች ለትንተና ከተመረጡት የጌትነት እንየው የተውኔት ስራዎች ላይ ማዕከል ተደርገው የተጠኑ ምርምሮችን ሲሆን ከምርምሩ የእይታ ማዕቀፍ ወይንም ንድፈ ሃሳብ አንጻር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች የምርምር ስራዎች ዳሰሳ ለማድረግም ሞክራለች፡፡

ከጥናታዊ ጽሁፌ ጋር እሚቀራረብ ሆኖ ያገኙኋቸው ጥናታዊ ጽሁፎች አንደኛው፣ ታሪካዊ እውነት አቀራረብ ‹‹በቴዎድሮስ ራዕይ›› በጊሩት አድማሱ (ዶ/ር) ባህርዳር ዩንቨርስቲ የተሰራ ጥናት ሲሆን፤ ሁለተኛው በእንግሊዝኛ ቋንቋ Tewodros in historical fiction በሚል ለአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ማስተር ኦፍ አርት ኢን ሊትሬቸር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ትምህርት በታየ አሰፋ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ ሦስተኛው በእጥፍወርቄ አደመ “የቴዎድሮስ ራዕይ" ታሪካዊ ድራማ ፣ “እቴጌ ጣይቱ" ታሪካዊ ድራማ” እና “ወይ አዲስ አበባ" ድራማ ከታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ተውኔት አኳያ በሚል ርዕስ በ2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ እና የመጨረሻው Presentation and Representation of History in “Etege Taytu” and “YeTewodros Haey” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በነብዩ ባዩ 2001 ላይ የተሰራ ጥናት ነው፡፡

1ኛ ታሪካዊ እውነት አቀራረብ ‹‹በቴዎድሮስ ራዕይ›› በጊሩት አድማሱ (ዶ/ር) ባህርዳር ዩንቨርስቲ ሂዩማኒቲ ፋካሊት በ2015 ለህትመት ካበቃቸው ጥናታዊ ፅሁፎች መሃል አንዱ ሆኖ አገኘቼ ተመልክቸዋለሁ። ጥናቱ በጌትነት እንየው የቴዎድሮስ ራዕይ” ታሪካዊ ተውኔት ላይ የተደረገ ነው፡፡ በጥናቱ ታሪካዊ እውነትን በተውኔት ውስጥ ለማቅረብ ጥቅም

ላይ የዋሉ ቴክኒኮች የተፈተሹበት ነው፡፡ ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ተውኔቱ ለመተንተን ጥቅም ላይ የዋለበት ሲሆን በተውኔት ውስጥ ታሪካዊ እውነት እንደምን ቀርቧል የሚለውን የተፈተሸበት ነው። ይህ ጥናት በንድፈ ሀሳብ ምርጫ እና የናሙና አመራርጥ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም የንድፈ ሃሳብ ጭብጦች እና በዚህ ጥናት ላይ የካሳ ፈረሶች መካተቱ ፍፁም የተለየ ያድርገዋል

2ተኛ. "ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታሪካዊ ልቦለድ"

ይህ ጥናት በእንግሊዝኛ ቋንቋ Tewodros in historical fiction በሚል ለአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ማስተር ኦፍ አርት ኢን ሊትሬቸር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ትምህርት በታየ አሰፋ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ ጥናታዊ ጽሁፉ ግንቦት 1980 ላይ ነው የቀረበው፡፡ የአቶ ታዬ አሰፋ ጥናት ስድስት ቂልፍ ጽሑፎችን ገምግሟል፡፡ ጥናቱ የተሰራባቸው የስነጽሁፍ ስራዎችም አንድ ለእናቱ፣ ጣይቱ ብጡል፣ ዋሪየ ርኪንግ፣ የቴዎድሮስ እንባ እንዲሁም በሎሬት ጸጋየ ገብረመድህን ቴዎድሮስና በግርማቸው ተክለኃዋርያት ቴዎድሮስ ተውኔቶች ነው፡፡ ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን የሴራ ግንባታ ላይ ትኩረት ያደረገና በአጤ ቴዎድሮስ ላይ የተንጸባረቁት ባህሪ ልዩነቶች እንዲሁም ከመገለጫዎቹ አንጻር ጥናቱ በፅሁፎቹ ውስጥ አጤ ቴዎድሮስ የተገለጡበት ባህሪ ላይ በስፋት ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ አጤ ቴዎድሮስ ጀግንነት፣ የለውጥ አቀንቃኝነት፣ጭካኔ፣ ላይ ጥኩረት ተድርጎ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ጥናት በሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ ጭብጦች ርዕዮተ አለም እና ማንነት ላይ ተመርኩዞ ጥንታኔ የሚሰጥበት መሆኑ ጥናቱን የተለየ ያደርገዋል፡፡

3ተኛ. በእጥፍወርቁ አደመ "የቴዎድሮስ ራዕይ" ታሪካዊ ድራማ ፣ "እቴጌ ጣይቱ" ታሪካዊ ድራማ" እና "ወይ አዲስ አበባ" ድራማ ከታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ተውኔት አኳያ በሚል ርዕስ በ2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ የምርምር ስራ ሲሆን ምርምሩ ትኩረቱን ያደረገው በሦስቱ ተውኔቶች ውስጥ የአገራችን ታሪክ እና ፖለቲካዊ ሁነቶች ምን ያህል ተንጸባርቋል? ነባራዊ ሁኔታዎችን ከመግለጥ አኳያስ ደራሲው ምንአይነት ቴክኒኮችን ተጠቅሟል የሚለውን ለመዳሰስ የሚሞክር ነው፡፡

4ተኛ Presentation and Representation of History in “Etege Taytu” and “YeTewodros Haey” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በነብዩ ባዩ 2001 ላይ የተሰራ ጥናት ሲሆን ምርምሩ ትኩረቱን ያደረገው የጌትነት እንየው ታሪካዊ የተውኔት ድርሰት በሆኑት እቴጌ ጣይቱ እና የቴዎድሮስ ራዕይ በተሰኙት ሁለቱ ተውኔቶች ውስጥ የተቀረጹት ታሪካዊ ገጸ ባህሪያት (እቴጌ ጣይቱ እና አጼ ቴዎድሮስ) ከነባራዊው ታሪካቸው አኳያ ደራሲው በተውኔቶቹ ውስጥ እንዴት አድርጎ እነዚህን የታሪክ አምድ የሆኑ መሪዎችን አቅርቧቸዋል የሚለውን በማገናዘብ መቃኘት አንደኛው ትኩረቱ ሲሆን ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ከታሪካዊ ተውኔት አጻጻፍ ቴክኒክ አኳያ ደራሲው ተውኔቶችን እንዴት አድርጎ በምን ቴክsኒክ አቅርቦታል የሚለውን ማስተንተን ላይ አጽንኦት ያደረገ ጥናት ነው፡፡ በመሆኑም እጥፍወርቄም የነብዩ ሁለቱም የጥናት ወረቀቶች ከእኔ የምርምር ርዕስ ጋር የሚያገናኛቸው አብይ ጉዳይ ቢኖር የናሙና አመራረጣችን ነው፡፡ በሦስታችንም የምርምር ናሙናዎች ውስጥ “የቴዎድሮስ ራዕይ” ታሪካዊ ተውኔቶች ከመገኘቱ ውጭ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም፡

## ምዕራፍ ሦስት፡- ትንተና

### የተውኔቶቹ አጽመ ታሪክ

### 3.1 የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" ታሪካዊ ተውኔት አጽመ ታሪክ

የቴዎድሮስ ራዕይ ሙዚቃ አቀፍ ታሪካዊ ተውኔት በ 2000 ዓ.ም ተጽፎ በሙሉዓለም የባህል ማዕከል እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ለእይታ የበቃ እና በቪዲዮም ተቀርጾ በሲዲ የተሰራጨ ተውኔት ነው፡፡ ተውኔቱ በ አምስት ትዕይንቶች የተከፋፈለ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጥንተ መሰረቷን መነሻ አድርጎ የቀደምት ታሪክ ባለቤትነቷ እና በስልጣን የንግስና ሽግግሩ ከአክሱም ወደ ላስታ፣ ከላስታ ወደ ሸዋ፣ ከሸዋ ወደ ጎንደር ከዚያም ወደ ዘመነ መሳፍንት የተሸጋገረበትን በሙዚቃ፣ በዘፈን እና በውዝዋዜ እያሳየ ይሄድና ከዛም አገሪቱ ቁልቁል የወረደችበትን ትዕይንት ያሳያል፡፡ በዘመነ መሳፍንት ተከፋፍላ ሃገር የሚያድናትን በምትሻበት ሰአት ‹‹የካሳን መነሳት›› ያሳየናል፡፡ ከካሳ መነሳት በኃላ ‹‹ፍቅር፣ አመጽና ድል›› (የካሳን እና የተዋበችን የልብ ፍቅር እንዲሁም ካሳ በእቴጌ መነን እና በራስ አሊ ላይ አምጾ መነሳቱን እና ድል አድርጎ እቴጌን እና የጦር መሪውን ምርኮ ማድረጉን ይነግረናል፡፡ ከዚህ በሓላም ካሳ ከፍ ብሎ ሁሉንም ድል እያደረገ ወደ ንግስና የሚመጣበት እና ኢትዮጵያን ወደ ጥንት ኃያልነቷ ከፍ ለማድረግ ራዕዩን በደማቅ ጽፎ እና በአዋጅ አስነግሮ የሚነሳበት፣ ሩጫ የሚጀምርበት፣ መሰናክል የሚበዛበት እና ከእንግሊዝ ጋር ጥል ውስጥ የሚገባበት ትዕይንት ያስመለክተናል፡፡ በየመጨረሻም ቴዎድሮስ የጦር መሳሪያ በአገር ውስጥ የማምረት ራዕዩ እውን የሆነበትን ሴባስቶፖል እና ሌሎችም መድፎቹ ተሰርተው መጠናቀቃቸውን እየነገረን የምስራች የሚሰሙበት እና ቴዎድሮስ መድፎችን ከሰሩ አውሮፓውያን ጋር ደስታ የሚለዋዎጥበት በመጨረሻም አጼ ቴዎድሮስ ከእንግሊዝ ጦር ጋር ፍልሚያ ውስጥ የሚገባበት እና ንጉሱ እጄን አልሰጥም ብሎ ሽጉጡን ጠጥቶ ራሱን በክብር ሞት የሚሞሽርበት ትዕይንት ያሳየናል፡፡ "የቴዎድሮስ ራዕይ" በዳግማዊ ቴዎድሮስ ወደ ስልጣን የመጡበትን መንገድ፤ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ያደረጉትን ትግልና መጨረሻቸውን የሚያሳይ ተውኔት ነው። ይህ ተውኔት ባህሪያቸውን፣ የአመራር ጥበባቸውን፣ የአንድነትና የክህደት ጭብጦችን በመዳሰስ ላይ ያተኩራል። አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የነበራቸውን ራዕይ ያንፀባርቃል፡፡ - የኢትዮጵያን

ታላቅነት ለመመለስ ጥረት ሲያደርጉና በመጨረሻ አሳዛኝ ፍጻሜያቸውን ያስከተለውን ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ያስመለክታል።

## 3.2 "የካሳ ፈረሶች" ታሪካዊ ተውኔት አጽመ ታሪክ

‹‹የካሣፈረሶች›› የዳግማዊ ቴዎድሮስን ትሩፋትና በዘመነ መንግሥቱ ላይ ስላሉ ታሪካዊ ክንውኖች የሚዳስሱ ተውኔቶችን እያሳየን የሳቸውን ምልከታ በተውኔት ውስጥ ባለ ተውኔት እንድናይ የሚያደርግ ተውኔት ነው። የሚች ኢትዮጵያውያን ሰማያዊ ጉባኤን በማቅረብ የሜታ ትያትር አካሄድን ይከተላል። ተውኔቱየ ቴዎድሮስን ስኬቶችና ውድቀቶች እሳቸውን ተመርኩዘው በተሰሩ ተውኔቶች ላይ እያሳየ የሚተቸውን በመተቸትና የሚደነቀውን በማድነቅ ክፍተቶችን እያሳየ በኢትዮጵያ ታሪክና በጊዜው በነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ አስተያየቱን ጭምር ይሰጣል። በአንደኛው ገፅታ የ19ኛው ክፍለ ዘመን ታሪካዊ ቅንጭብጭብን የሚያሳይ ሲሆን በሌላኛው ክፍል ደግሞ ተራኪው ታዳሚውን የሚመራበት ነው። ታሪኩ የሚያጠነጥነው ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ (ካሣ) እና እቴጌ ተዋበች ከሞት ተመልሰው ወደ ምድር በመምጣት ዘመናዊት ኢትዮጵያን ተመልክተው ለመመስከር መመረጣቸውን በማሳየት በመጀመር ነው፡፡ ንጉሱ የተመረጡት ኢትዮጰያን በ200 አመት ታሪክ ውስጥ ከገዙ ነገስታት እና መንግስታት መካከል በአብላጫ ድምጽ አግኝተው ነው፡፡ በመመረጣቸው ወደ አዲስ አበባ ለ24 ሰአት ቆይታ ይመጣሉ። አጤ ቴዎድሮስ ከ160 አመታት በኃላ ኢትዮጰያ መጥተውም ትተውት የሄዱትን ታሪክ ለመመልከት ሲታደሉም ብቻቸውን መምጣት አልፈለጉም ነበርና የተሰጣቸውን መብት ተጠቅመው ባለቤታቸውን አስከተሉ፣ የሚመለከቱትን ታሪክ እንዲተርክ ወጋየሁ ንጋቱንም አስከተሉ፣ በሰው የአሁኗ ኢትዮጰያ ስለተቀየረች በጉዟቸው የሚያጫውታቸው አዝማሪም አስከተሉ፡፡፡ ወደ አዲስ አበባ ከመጡም በኃላ በተዋናይ ታጅበው ታሪክ በምን መልኩ እያወሳቸው እንዳለ ለመመልከት በእርሳቸው ላይ የተሰሩ የተለያዩ ድራማዎችን ለመመልከት ብሔራዊ ቴአትር ይገኛሉ። በህይወት ታሪካቸው ላይ ተመርኩዘው የተሰሩ የተለያዩ ተውኔቶችንም ይመለከታሉ። ስለ ትሩፋቶቻቸው፣ ስለ ድሎቻቸው እና ውጣውረዶቻቸው ታሪክ እንዴት እንዳወሳቸው በተውኔቶቹም ውስጥ ይመለከታሉ። በሚመለከቷቸውን ተውኔቶችም በትክክል ሃሳብ መግለጣቸውን መዛባታቸውን እዛው ፊት ለፊት ሆነው ሃሳብ ይሰጡበታል፡፡ ተውኔቶቹ እንደየ ዘመናቸው የተለዋወጡና

የመንግስታቱን የአገዛዝ ባህሪ የተላበሱ እንደሆኑም ይጠቁመናል፡፡ ኢትዮጲያ ያለችበትን ሁነት በብሄር እና በክልሎች ግዛት መከፈሏን፣ የቋራ ምድር ለሱዳን ተላልፎ በመንግስት ፈቃድ መሰጠቱ ይነገራቸዋል፡፡ ነግራችሁኝ ሳይሆን ቋራን በአይኔ ተመልክቼ ነው የማምነው በማለት ለመሄድ ሲነሱ ተውኔቱ ያበቃል፡፡

## 3.3 ርዕዮተ አለም በተውኔቶቹ ውስጥ እንዴት ተንጸባርቋል

### 3.3.1 "የቴዎድሮስ ራዕይ" ተውኔት ውስጥ

ተውኔቱ በተጻፈበት ዘመን በገዢው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ስር ያለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ልማታዊ መንግስት የሚል ነው፡፡**የልማታዊ መንግስት ሞዴል** መንግስት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እና ድህነት ቅነሳ ላይ ትኩረት በማድረግ ኢኮኖሚውን በመምራት ማዕከላዊ ሚና ይጫወታል። የልማታዊ መንግሥት አንዱና ትልቁ መነሻው ኅብረተሰቡ የሚጋራው ልማታዊ ራዕይ ያለው መሆንና ኅብረተሰቡን ለዚህ ራዕይ መሳካት በተደራጀ መልኩ ማንቀሳቀስ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከምትገኝበት አገራዊ ሁኔታ አኳያ አገሪቱን ከድህነት ማውጣትና ወደ መካካለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ተርታ ማሠለፍ የሚቻለው፣ ሕዝቦች በየአካባቢያቸው ወደ ልማት ማስገባት ሲቻል ነው፡፡(Berhe, A፣ 2008)

ልማታዊ መንግስትም በዓላማው ጠንካራ መካከለኛ ገቢ ያለው ዜጋ መፍጠር ነው፡፡ የልማታዊ መንግስት ሌላው ባህሪይ እርሱ በሚያስበውና በሚያልመው መንገድ ብቻ ነገሮች እንዲሄዱ የመፈለግ ችግር ነው። በልማታዊ መንግስት ከሚያስተዳድረው ህዝብ ፈቃድን አይጠይቅም። ልማት ያመጣሉ ብሎ የሚያስባቸውን ነግሮች ሁሉ በራሱ እንዲፈጸሙ ያደርጋል። (Clapham , 2018)፡፡

ስነ-ጽሁፍ የተፈጠረው በባዶ ነገር ላይ ሳይሆን በጊዜው ከነበረው ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ተለዋዋጭነት ጋር በእጅጉ ተቆራኝቶ ነው። (Foucault,1980)፡፡ ስነ-ጽሁፍ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚታየው የርዕዮተ ዓለም ሞገድ ጋር በጥልቅ የተሳሰረ፣ በጊዜው የተፈጠረ ውጤት ነው፡፡ (Althusser,1970)፡፡ የአልቱሰር ISA ንድፈ ሃሳብም ስነጽሁፉ በተፈጠረበት ዘመን ያለው ርዕዮተ አለም የግለሰቦችን እምነት በመቅረጽ ተፈጥሯዊ ወይም

የማያጠራጥር አድርጎ በማቅረብ ህብረተሰቡን  በራሳቸው መገዛት ውስጥ ተባባሪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ገፀ-ባህሪያት አንዳንድ አስተሳሰቦችን በሚያንፀባርቁ ወይም በሚያስፈጽም መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ ይላል።

ከዚህ አንጻር ቴዎድሮስን እንደ ዘመናዊነት መቀስቀሻ አድርጎ በመጠቀም በመቅረጽ፣ ጽሑፉ በመንግሥት የሚመራውን ኢንደስትሪላይዜሽንና የትምህርት ማሻሻያዎችን ሕጋዊ ለማድረግ ይጥራል፡፡ የቴዎድሮስን የልማት አርበኛ አድርጎ በማቅረብ ታሪክን በመንግሥት ፕሮፓጋንዳ ውስጥ አስገብቶት እናገኛለን። በቴዎድሮስ ራዕይ ላይም አጤ ቴዎድሮስ ለህዝቡም ለሃገርም ያስፈልጋል ብለው ያሰቡትን ለውጥ እና ልማት በራሳቸው ለማስፈጸም ከላይ በተገለጸው መልኩ ሲታገሉ ይታያል፡፡

"የቴዎድሮስ ራዕይ " ላይ  አጤ ቴዎድሮስ ሌላኛው የተወከሉበት መንገድ የሃገርን አንድነት አስቀጣይ ሆነው ነው፡፡ በጣም ጠንካራው ጭብጥ የሀገር ፍቅር አንድነት ነው። በተውኔቱ ውስጥ የተገለጸውን ይህንን ሃሳብ በዘመኑ ከነበረው ርዕዮተ አለም ጋር በትይዩ ስንመለከተው ኢህአዲግ በህገ መንግስቱ የኢትዮጵያን የብሄረሰቦች ብዝሃነት ተቋማዊ በማድረግ በብሄር የተቀመጡ ክልሎችን የፈጠረበት ነው። ከዚህ አንጻር አጤ ቴዎድሮስን በቴዎድሮስ ራዕይ ላይ እንዴት እንደተወከሉ ስንመለከታቸው በዋናነት ወደ ትግል ያስገባቸው ጉዳይ በሃገራቸው መገፋት፣ መሳደድ እና በማንነታቸው ላይ የተሰነዘረባቸው ጥቃት ነው፡፡

> "… እነካሣ ናቸው፡፡. . . በገዛ አገራቸው፣ መጠቃቱ፣ መገፋቱ ቢያስከፋቸው፣ የሀገራቸው መከራ፣ የወገናቸው ፍዳ ከያሉበት ሁሉንም አፈላልጎ፣…ገብርየን ከጋይንት መቀስ ተራራ፤ ገልሞን ከጭልጋ ማርቤቲ፤ አለሜንና ካሣን ከቋራ በአንድ መንፈስ አሰባስቦ፣ ለአንድ አላማ ያቆማቸው፤ … " (የቴዎድሮስ ራዕይ ገጽ፣5)
>
> "…ገብርዬ
>
> ይኸውልህ እንግዲህ፣ ይኸ ከንቱነታቸው ነው ህሊናዬን ያሳተኝ፡፡ የማር ውሃ አባት፣ "ልጄን የማንም አጥንተ ሰባራ ከሚያገባት፣ ከመቃብር በታች ውላ፣

ዛሬውኑ የጋይንት ምስጥ¸ ይብላት አሉ ማለትን ስሰማ፣. . . ይኸው ይኼ ጨለማ አይንጋልኝ አጋንንት እንደሰፈረበት ሰው ነው እረፉ ያስደፈቀኝ ... እንደዛር የሠራ አካላቴን እያንዘፈዘፈ ከመሬት ላይ ጥሎ፣ አጋንንት እንደሰፈረበት ሰው ነው፤እልህ አረፉ ያስደፈቀኝ፡፡...” (የቴዎድሮስ ራዕይ ገጽ፣11)

በተውኔቱ ውስጥ ከላይ እንደተገለጸው ካሳን፣ ገብርየን፣ ገልሞን እና አለሜን ያሰባሰባቸው ይህ በማንነታቸው የተቃጣ ጥቃት እና ያልተከበረላቸው መብት መሆኑን ያሳያል፡፡ በማንነት ፖለቲካ ላይ ከላይ እንደተመለከትነው ቡድኖች ልዩነታቸውን ያጠብቃሉ በአንድ ለመሰባሰብም እድልን ያገኛሉ። ገብርዬን እንዲህ መጠቃቱ ያንገበገበውን ያህል ካሳን ተዋበች ተነስ ብላ ስታስታጥቀው በማንነቱ የመጣበትን ጥቃት ራሱ እንዲመክት በማሳሰብ በማጀገን ነው፡፡

... ተዋበች /በንዴትና በቁጣ ትከሻዋን ከእጁ መንጭቃ እየተንጐራደደች/. . . ምን አርግ የምልህ ይመስልሃል ካሳ?. . . ተነስ ነዋ የምልህ፣ .. ተነሳ! .. ገና. . . ከጋሜነት ጀምሮ ከጥቃት ሞት እንደምመርጥ አሳምረህ ታውቀኛለህ፡፡ ዛዲያን ዘመዶቼ እነሱው ባሳደዱን፣ እነሱ ባዋረዱን፣ እነሱው በሰደቡን፣ እነሱው በበደሉን እነሱው እንደተበዳይ፣ የግርምቢጥ ጦር ሲሰብቁብን ምን የምልህ ይመስልሃል? ... ምነው ካሣ? ከፈሪ ጋር ከምኖር ከጀግና ጋር መሞትን እንደምመርጥ እያወቅህ እኮ ከሰው ሁሉ ተመርጦ፣ ያውም ወንድይራድ ይዝመትብህ!. . .እንኳን ገብርየን መሳይ፣ እንኳን አለሜን መሳይ፣ እንኳን እነ ገልሞን መሳይ ነብሮች ይዘህ አንድ ብቻህን የምትሰራውን አውቀዋለሁ ታውቀዋለህ፡፡ ዛዲያን ምን የምልህ ይመስልሃል? ተነስ

ነዋ የምልህ! በላ ተነሳ ... በላ ታጠቅ ካሣ...(ገጽ፣25)

በመሠረቱ የማንነት ፖለቲካ ዓላማ የተለያዩ ማንነቶች እኩል የሚስተናገዱበት ሥርዓት መፍጠር ነው፡፡ በእዚህም የፖለቲካ ሥርዓቱን ከቅራኔ በማላቀቅ የማኅበረ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ዕድገት ለማምጣት መሠረትና መደላደል የሆነውን የፖለቲካ መረጋጋት መፍጠር ነው፡፡ ኢህአዴግ የሚከተለው የማንነት ፖለቲካ የተጨቆኑ በማንነታቸው የተገፉ ላላቸው ወገኖች እኩል መብትን መስጠት ነው፡፡ (Lefort, 2013):: በተውኔቱ ውስጥ ካሳ

እና ጓደኖቹ የሚታገሉለትን የእኩልነት ጥያቄ ያስከበረ አድርጎ በጊዜው የነበረው መንግስት ኢህአዴግ ለፕሮፖጋንዳ ተጠቅሞበታል፡፡

የርዕዮት ዓለም ስነ ጽሁፍን እንደ መሣሪያ እንድም ለመገንባት አንድም ለማፍረስ ይጠቀምበታል፡፡ (Althusser, 1970)፡፡ ርዕዮተ ዓለም ከኃይል ጋር በቅርበት የተሳሰረ ነው። ብዙውን ጊዜ የገዢ ቡድኖችን ጥቅም በማስጠበቅ ሌሎችን እያገለለ ያለውን ሁኔታ ለማስረዳት እና ለማስጠበቅ ያገለግላል። ርዕዮተ ዓለምን መረዳት ከተወሰኑ ማህበራዊ አወቃቀሮች እና ትረካዎች ማን እንደሚጠቀም ለማወቅ ይረዳል። ርዕዮተ ዓለም እንዴት በኃይል መዋቅሮች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ሥነ-ጽሑፍ ሊገልጽ ይችላል። በገጸ-ባህሪያት እና ሴራዎች ደራሲዎች የጭቆና፣ የተቃውሞ እና የማህበራዊ ፍትህ ጭብጦችን ያስተላልፋሉ፡፡

ከዚህ አንጻር አጤ ቴዎድሮስን በቴዎድሮስ ራእይ ውስጥ ለውድቀት ያበቃቸው በየ አካባቢው የሚነሱ ገዥዎችን በቆራጥነት እና በጭካኔ አንድነትን ለማምጣት የወሰዱት እርምጃ እንዲከዷቸው እንዲነሱባቸው ማድረጉ ነው፡፡ በተውኔቱ ጠንካራ ማእከላዊ መንግስት መመስረት ለሃገር ዋስትና ለአንድነቷም የጸና መሰረት መሆኑን ይነግረን እና የየአካባቢው የግዛት አስተዳዳሪዎችን መብት አክብሮ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት አለማስከበር ለውድቀት እንደሚዳርግ ይሰብክበታል፡፡

"ካሣ

ምን ላድርግ ተዋቡ? . . . ወዴት ልጩህ? ለማን ላልቅስ? . . . አደራውን ተቀብዬ፣ ከአገር አገር እየተንከራተትሁ፣ አገር ላቀና በደከምሁ፣ ፍትህ ላሰፍን በዋተትሁ፣ አንድ ነበርን አንድ እንሁን፣ ትልቅ ነበርን ትልቅ እንሁን ብዬ በቃተትሁ፣ ቴዎድሮስ ምን አጠፋሁ?

ተዋበች

አንተ ምንም አላጠፋህ ጌታዬ" (ገጽ፣34)

"ተራኪ

ያ እንደንብ መንጋ ሲተም፣ በሚያስነሳው አቧራ ብቻ ጠላትን ያርድ የነበረው የቴዎድሮስ ወታደር፣ ዛሬ በመሳፍንቱ ድለላ፣ በቀሳውስቱ ግዝትና ሰበካ ከድቶ፣ አልቆ፣ ...ያ ቁጥሩ መቶ ሺ እንኳ የማይጠቀመው ሰራዊት፣ ዛሬ በቅጡ ሰባት ሺህ መሙላት እንኳ ተስኖት እየታየ ... ቴዎድሮስ ብቻውን መቅረት ከጀመረማ ቆዬ ..." (የቴዎድሮስ ራዕይ ገጽ 51)

በቴውኔቱ ውስጥ አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመታደግ ራሳቸውን ለመስዋትነት ያቀረቡ ቆራጥ መሪ አድርጎ ያቀርባቸዋል፡፡

በኢህአዴግ ጊዜ የነበረው ርዕዮት አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሲሆን በመንግሥት መሪ ፍልስፍና አገላለጽ የገጠሩ አርሶ አደር የራሱን እጣ ፈንታ ለመወሰን ብቁ ያልሆነና በተቃራኒው 'ያልተማረ '፣በ ' ኪራይ ሰብሳቢዎች ' ለመጭበርበር ተጋላጭ የሆነና በዚህም ምክንያት የመንግሥት 'ጥበቃ ' እንደሚያሻው ተደርጎ  የሚቆጠር ነው፡፡ (Lefort, 2013)፡፡  ይህ ሃሳብ በተውኔቱ ውስጥ "የቴዎድሮስ ራዕይ" ላይ አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ህዝብን የሚታደገው የእርሳቸው የልማት ራዕይ፣ ዕውቀትን መሻትን፣ አንድነትን ሲያመጡ እንደሆነ ያንጸባርቃል፡፡

## 3.3.2 ርዕዮተ አለም "የካሳ ፈረሶች"ውስጥ

"የካሳ ፈረሶች"ታሪካዊ ተውኔት በነሃሴ ወር 2009ዓ.ም ለህትመት የበቃ እና በ2011 ዓ.ም ለዕይታ የበቃ ተውኔት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ ትልቅ የርዕዮተ ዓለም እና የፖለቲካ ለውጥ ምልክት ነበረበት። ይህ ሽግግር የጀመረው በየካቲት 2010 በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ስልጣን መልቀቂያ አስገብተው ሚያዚያ 2010 ዓብይ አህመድ ወደ ስልጣን ሲወጡ ነው። ወቅቱም የለውጥ አራማጆች ትረካዎች ከኢህአዴግ ያለፈ አስተሳሰብ መላቀቅ እና አዳዲስ ፖለቲካዊ እና አገራዊ ንግግሮች የታዩበት ነበር።

የ2010 የሽግግር ወቅት ርዕዮተ ዓለማዊ ለውጦች እና ትረካዎች እና የጠ/ሚኒስትር አብይ አህመድ(ዶ/ር) ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ መላቀቅ፣ የፓርቲ የበላይነትን፣ በመንግስት የሚመራ ልማት እና የብሄር ፌደራሊዝም ላይ አፅንዖት ሰጥቷል።አዲሱ አመራር የቀድሞውን ስርዓት አምባገነን ፣ከፋፋይ እና ሙሰኛ ሲል ተችቷል። አዲሱ ዘመን የዲሞክራሲ፣ የአንድነት እና የሊበራል ተሀድሶ እንደሚሆን ቃል ገብቷል።

"የካሳ ፈረሶች" የእንዳለጌታ ከበደ በ2009 ዓም የታተመ ተውኔት ሲሆን ተውኔቱ በተፈጠረበት ዘመን የነበረውን ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁነት እንዴት እንዳንጸሃረቀ እና በጊዜው የነበረው ርዕዮተ አለም እንዴት እንደተንጸባረቀ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ተውኔቱ በታተመበት በ2009 ዓ/ም ነሃሴ ወር አገራዊ አንድነት እና የተቃውሞ ንቅናቄዎች የተፈጠሩበት ጊዜ ነበር። የኢሃዴግን አገዛዝ በመቃወም የኦሮሞ እና አማራ ወጣቶች አንድነትን የፈጠሩበት ጊዜ ነው፡፡( Tareke, G. 2009)፡፡

"የካሳ ፈረሶች" ተውኔት ዳግማዊ ቴዎድሮስን ከ200_300 አመታት ከነገሱት ነገስታት ሁሉ የተመረጡ አድርጎ ይስላቸዋል።

> "...ኢትዮጵያውያን በአንድ ታላቅ አዳራሽ ውስጥ ተገናኝተው፤ ኢትዮጵያን አስተዳድረው ከነበሩ ነገሥታት መካከል፣ አብልጠው የሚወዷቸውን እንዲመርጡ ተደረገ፡፡ ምርጫውም ያለአንዳች ቅሬታና ግርታ ተከናወነ፡፡ በአስገራሚ ሁኔታ በሃይማኖት አባቶች ፣ በአገር ወዳድ ዜጎችና በተራ ሟቾች ዘንድ አጼ ቴዎድሮስ -መይሳው ካሣ አባ ታጠቅ ብዛት ያለው ድምጽ አገኙ፡፡ ውጤት በተገለፀ ጊዜም ጭብጨባው ሎኘ፡፡ ዕልልታው ደመቀ፡፡..."(የካሳ ፈረሶች ገጽ፣226)

ተውኔቱ ለህትመት በበቃበት ጊዜ "የኦሮሞ ደም ደሜ ነው" (Awol Kassim፣ 2016) በሚል የጎንደር ህዝብ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት ስለ ኢትዮጵያዊነት እና አንድነት በአደባባይ የሰበከበት ጊዜ ላይ ነው እንዳለጌታ ከበደ በተውኔቱ ለህትመት ያበቃው ።

ተውኔቱ የለውጥ ንቅናቄ ላይ እንደመፈጠሩ ታሪክ የተላለፈበትን መንገድ ይሞግታል። አጤ ቴዎድሮስን በአንደበታቸው ስለ እሳቸው የተሰሩ ተውኔቶችን በመመልከት በተውኔት

ውስጥ ባለ ተውኔት እንዲተቹት ያደርጋቸዋል። ታሪክን በማጉደፍ እና በማዛባት የተላለፉ ለግጭት መንስዔ የሆኑ እውነቶች ይተቻሉ።

"...ተዋበች፤ አገሪቷ ዳኛም የላት እንዴ፣ እንዲህ

በአንደበትዎ ሲናገርበት ማንም _ እየተነሣ..."(ገጽ፣233)

"... መቼም መቅደላ ተራራ ላይ ወጥቶ ክንፍ አበቀለ፤ ወደ ሰማይ አረገ ብሎ አይጽፈኝ አይጽፍልኝ!!" (የካሳ ፈረሶች ገጽ፣236)

የኢትዮጵያዊነት አንድነት ስሜትን የሚያበረታቱ አገር ፍቅርና አንድነትን እንደ ዋና እሴት የመግለጽ አዝማሚያ ያለቸው ሃሳቦች ተንፀባርቀውበታል። ጠ/ሚ አብይ ጎንደር ላይ በ2010 ያደረጉት ንግግርም ኢ.ቢ.ሲን ጨምሮ ሁሉም ሚዲያዎች በቀጥታ ያሰራጩት መልክት

" ... ለሃገራችሁ እና ለህዝባችሁ የምታሳዩት ፍቅር፣ ለቃላችሁ የምትሰጡት ክብር እና በአገር አንድነት ላይ ያላችሁ ጽኑ አቋም ሁሉም ኢትዮጳያዊ ዘላለም ያከብረዋል፡፡ . . . በየዘመናቱ እና በየመንግስታቱ የሚገጥማችሁን ፈተናዎች የምትሻገሩበት ትዕግስት ወኔና ጥንካሬ እንዲሁም ከሁሉም ኢትዮጳያዊ ወንወድሞቻችሁ ጋር ያላችሁ የማትደራደሩበት አሴት ሁሌም እንዳስደመመ ዛሬም ቀጥሏል፡፡ የዘመናዊቷ ኢትዮጳያ ጠንሳሽ የመይሳው ልጆች. . . ዘመኑ የሚጠይቀው ጀግንነት ራስን እና አካባቢን መቀየር "

መንግስት የኢትዮጵያ ጀግንነት በየዘመኑ እንዳለ እና ዘመኑን ያዋጅ መሆን እንዳለበት አፅንኦት ያንጸባረቀው ርዕዮት በተውኔቱ ላይ ተገልጾ እንመለከቷለን።

" ካሣ፤ ምን ነካሽ ተዋበ፣ ጀግና ለመባል የግድ እጄን ለጠላት አሳልፌ ከምሰጥ በሎ ሽጉጥ መጠጣት አለበት? ... ማየት የመፈለግና ልብ የማለት ችግር ነው'ንጂ እያንዳንዱ ዘመን የሚመጥነውን ጀግና አፍርቶ ያልፋል የግድ መሪ መሆን አይጠበቅበትም፡፡ በኢኮኖሚ በልፅገ ድህነትን አሸንፎ መኖር ጀግንነት ነው፤ ከሞት ጋር ተናንቆ ለመኖር መፍጨርጨርም

ጀግንነት ነው፤ የሚወዱትን ሥራ ሰርቶ ማደርም ጀግንነት ነው፤ ጀግንነት ማለት'ኮ ምንም ማለት አይደለም፤ መሆን የምንፈልገውን እንዳንሆነው የሚገዳደረያን ጠላት ታግሎ መጣል ነው እንጂ። ላለመውደቅ መንገዳገድ!

ተዋበች፤ [ካሣን በፈገግታ እያዩ] እኔማ እነዚያ እንግሊዞች፣ ከቀለበትዎና ከሐብልዎ ጋር ከመጽሐፎችዎ ጋር ወስደውት ይሆን እላለሁ፡፡

ካሳ፤ ምኑን?

ተዋበች፤ ሱሪዎትን ነዋ፤ የወንድነትዎን ትጥቅ፣ የጀግንነትዎን ልክ፣

ካሣ፤ ተይ ተዋቡ! የካብሺኝ መስሎሽ ለምን ትንጂኛለሽ? ታናጅኛለሽ፡፡ እኔም፣ ዮሀንስም፣ ምኒልክም ሁላችንም ከዘራነው በላይ አብቅለናል፡፡ ወንድ አስታጥቀናል ነው የምልሽ፡፡ አንድ ብቻ አታርጊኝ፡፡ አንድ ሲያረጉኝ ያመኛል፡፡ በእርግጥ አንድ ነኝ ለእናቴ፡፡ እኔ ከወጣሁበት ማኅፀን ቀድሞኝም ሆነ ተከትሎኝ የወጣ የለም፡፡ አሁን ግን በዝቻለሁ፡፡ ብቸኛ ወንድ ሲሉኝ ይከፋኛል፡፡" (የካሳ ፈረሶች ገጽ፣ 249-250)

በኢህአዴግ ዘመን የነበረውን ርዕዮተ ዓለም ይወቅሳል። የኢህአዴግ ፌደራላዊ ስርዓት የክልል ራስን በራስ የማስተዳደር እና የባህል ብዝሃነትን ከብሄርተኝነት ይልቅ የኢትዮጵያዊነት ስሜትን ማዳበር እንደሚያስፈልግ ይህ የሚያመለክተው እውነተኛው የቀጣይ መንገድ ተጨማሪ የጎሳ ፌደራሊዝም ሳይሆን ቴዎድሮስ ያመለከተዉ የሀገር ፍቅር አንድነት መሆኑን ነዉ።

"... በነገራችን ላይ የቴአትሩን ሙሉ ወጭ የቻለው የአማራ ክልል ብሔራዊ መንግስት...ነው። የሚያሳዝነው ለሦስት ቀናት ብቻ ነው የተሠራው።

ካሳ፤ እህሃ የኢትዮጵያው የት ሄዶ ነው?

ተራኪው፤ አላወቁም እንዴ እስካሁን ጃንሆይ?

ተዋበች/ካሳ፤ ምኑን?

ተራኪው፤ በዝተዋል እኮ ጃንሆይ በዝተዋል የአፋር መንግስት፣ የሲዳማ መንግስት፣ የኦሮሚያ መንግስት በዝተዋል እኮ

ካሳ፤ በርትተዋላ" (የካሳ ፈረሶች ገጽ፣247)

## 3.4 ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ

### 3.4.1 ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ "የቴዎድሮስ ራዕይ" ተውኔት

"የቴዎድሮስ ራዕይ" በጌትነት እንየው የተዘጋጀ ሙዚቃዊ ተውኔት ሲሆን ተውኔቱ ጥቅምት ወር ላይ 2000 ዓም ለእይታ የበቃ ነው፡፡ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና የኢትዮጲያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር ጽ/ቤት የተዘጋጀ ነው፡፡ ተውኔቱ በጊዜው የነበረውን የመንግስት ርዕዮተ አለም እና በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ እንዴት እንደሚያንጸባርቅ እንመልከት፡፡

ተውኔቱ የኢትዮጲያ ሚሊኒየም በዓል በሚከበርበት ጊዜ ላይ የተዘጋጀ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከምትታወቅባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የራሷ የቀን መቁጠሪያ ያላት መሆኗ ነው፡፡ ይህ በታሪክ ትልቅ ስፍራን የተሰጠው የሚሊኒየም በአል በጊዜው በነበሩት ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በሚሊኒየም አዳራሽ ‹‹መጪው ዘመን የኢትዮጵያ ህዳሴ ይሆናል!!›› የሚለው የዋዜማ ንግግር የተከፈተ ነበር፡፡ ከዓለም ታላላቅ ስልጣኔዎች መካከል የነበረችበትና በሂደትም ፀጋዋን በአግባቡ መጠቀም ባለመቻሏና ቀደሞ የነበራት ዝናና ገናናነት በሂደት እያሽቆለቆለ የኋሊዮሽ ጉዞን ያሳለፈችበት ወቅትም ነበር፡፡ የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በሚሊኒየም አደራሽ ባደረጉት ንግግር ‹‹ላለፍንበት ሁኔታ ተጠያቂዎቹ እኛና እኛው ብቻ ነን፡፡›› በሚል ያስቀመጡት ሀሳብ ኢትዮጲያ ወደ ቀድሞው ገናናነት ዘመኗ ዳግም የመመለስ ጉዞ የህዳሴ (renaissance) እቅድ ከዚህ እልህና ቁጭት የሚነሳ ነው፡፡ ከዚህ በጊዜው የነበረው ርዕዮተ አለም እና የማህበራዊ ፖለቲካዊ ሁነት አንጻር "የቴዎድሮስ ራዕይ" ተውኔት ውስጥ ይህ እንዴት እንደተገለጸ ከሃዲስ ታሪካዊ ሂስ አንጻር እንመልከት፡-

ሃዲስ ታሪካዊ ሂስ የስነጽሁፍ ስራዎች በዘመኑን መቀረጽ እነሱም በፈንታቸው ዘመኑን የመቅረጽ አቅም አላቸው፡፡ ይህም ስራው ከተጻፈበት ዘመን አውድ አንጻር ሊታይ ይችላል (Habib,2005)፡፡ ከዚህ አንጻር "የቴዎድሮስ ራዕይ" ተውኔት ለእይታ በበቃበት ጊዜ ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጰያ ጥንተ መሰረት ገናናነት በስፋት ይነገርበት የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡

"የቴዎድሮስ ራዕይ" ላይ ተራኪው ኢትዮጰያ ገናና የነበረች ሃገር መሆኗን በመጥቀስ የቁልቁለት ጉዞዋን ይተርክልናል

> … ይህቺ ሀገር፣ ይህቺ ኢትዮጵያ፣ ሩቅ ነው ስር መሰረቱዋ! ልሂቅ ነው ወርድ ስፋትዋ!. . . አዎ፣ በምስራቅ፣ እስከማዳጋስካር፣. . . በደቡብ፣ እስከ ኒያንዛ ባህር፣ . . . በምዕራብ እስከ ኑቢያ፣ በሰሜን እስከ ምድር፣ . . . የተዘረጋ ቁመትዋ፣ የተንጣለለ ደረቱዋ፣ . . .፣ ይህቺ ባለጥንት ታሪክ ባለቀደምት ስልጣኔ፣ ይህቺ ባለድንቅ እደ ጥበባት ሀገር፣ . . . ሩቅ ነው ስርወ ግንድዋ! ጥብቅ ነው ዘር ሃረግ ውሉዋ! ጥልቅ ነው መሰረት ስርዋ!! . . . (የቴዎድሮስ ራዕይ ገጽ፣ 1)

የሐዲስ ታሪክ ሊቃውንት የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ከታሪካዊ ጊዜያቸው የማይነጣጠሉ ናቸውይላሉ፡፡ ስለዚህ ጽሁፉን በተፈጠረበት አውድ ውስጥ መቀመጥ አለበት (Greenblatt, 1980)

ከዚህ አንጻር ተውኔቱ የተፈጠረበትን ዘመን ማህበረ ፖለቲካዊ ሁነት ስናየው ይሄ ተራኪው የሚገልጸው ታሪክ በኢትዮጵያ ሚሊኒየም የመንግስት ባለስልጣናት፣ ሚዲያዎች ጭምር ያቀነቅኑት ይናገሩት የነበረው ሃሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡ በተለይም የራሷ ቀን መቁጠሪያ ያላት ሃገር እንደመሆኗ ከሌላው አለም በተለየ መልኩ የሚሊኒየምን በአል ስታከብር ከታሪክ ጋር ያለው ቁርኝት በስፋት ይገለጥ ነበር፡፡ (Bekele Mekonnen, 2000, ethio.post)

በተውኔቱ ውስጥ የተካተተውን አክሱማዊት ሃበሻየ የሚል ህብረ ዝማሬን ስንመለከትም፡፡

ታሪካዊት - መነሻዬ

ሀገራዊት - መድረሻዬ

የዘር ሃረግ - ማሰሪያዬ

አክሱማዊት - ሃበሻዬ (የቴዎድሮስ ራዕይ ገጽ፣ 2)

አክሱምን ገናናነት መነሻ አድርጎ በተውኔቱ ውስጥ የተሰራው "አክሱማዊት አበሻዬ" የሚለው ህብረ ዝማሬ በጊዜው ኢትዮጵያን የሚያስተሳስር አንድ የሚያደርግ የኃላ ታሪክ የሚፈለግበት ጊዜ ከመሆኑ ባለፈ በ1929 ዓም በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ጊዜ ከኢትዮጲያ ወደ ጣሊያን ተነቅሎ የተወሰደው የአክሱም ሃውልት ዳግም ወደ ኢትዮጲያ የተመለሰበት ጊዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጋራ ታሪክን ከፍ ብሎ ለማቀንቀን የተመቸ ነበር:: የሚሊኒየሙ አከባበር ምን ያህል የሁሉንም ኢትዮጲያውያን እና የብሄር ብሄረሰቦችን ስሜት አንጸባርቋል የሚለው በተመለከተ Forging a nation: The Ethiopian millennium celebration and the multiethnic state በሚል በIzabela anna Orlowska የተሰራው ጥናት አንዱ ለሚሊኒየም በዓል ዝግጅት ብሄራዊ ስሜት መቀንቀን የአክሱም ስልጣኔ ከሃውልቱ መመለስ ጋር ተያዞ የአንድነት ስሜትን እንዳቀጣጠለ ይነግረናል፡፡

> "… The millennium year conveniently coincided with the return of an Aksumiteobelisk, removed by Fascist Italy in 1937 during its brief occupation of thecountry. After years of negotiations between the Italian and Ethiopian gov-ernments, in April 2005 the 1700-year-old obelisk returned from Italy, whereit had stood near the Circus Maximus in Rome. Seizing the opportunity, theMillennium Council insisted on re-erecting it in the millennium year. Theunveiling celebration in Aksum was subsequently scheduled for 4 September2008, as the last in the series of millennium-year events. Despite pleas fromarchaeologists, who had recently discovered a network of underground tombsbeneath the original site, the plans to re-erect and unveil the monumentcontinued.9The possibility of

> damage to the obelisk itself during its re-erectionand the necessity to fill the underground chamber with cement in order toprovide a suitable foundation did not deter the authorities and the projectwent ahead. Consequently, the new structure destroyed the possibility ofexcavations on that site forever. Clearly, the symbolic value of the Aksumiteobelisk and its usefulness for the millennium project meant more than learningabout ancient Aksum itself'' (Izabela Orlowska,2023)

" አክሱማዊት ሃበሻዬ" የሚለው በተውኔቱ ውስጥ የተገለጠው ህብረዝማሬም ይህንን በጊዜው የነበረውን ስሜት የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

" የቴዎድሮስ ራዕይ" ላይ በተራኪው ገጸ ባህሪ የተነገረው ሌላኛው ሃሳብ አጼ ቴዎድሮስ ከመነሳታቸው በፊት በታሪክ ገናና የነበረችው ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ተከፋፍላ ከማንነት ክብሯ ወርዳ የወደቀችበትን ጊዜ በቁጭት ይተርካል፡፡

> " በእኔ እጎርስ፣ እኔ እጎርስ ስስት፣ ተበጣጥቆ፣ ተቦጫጭቆ፣ ተፍረክርኮ የታየበት፣ . . . አንድ ትልቅ የነበረች ሀገር፣ በየወንዙ ተሸንሽና፣ በየሰላሳው ሹም ስር፣ ሰላሳ ትንንሽ ሆና፣ . . . ቁልቁል የወደቀችበት፣ ህዝቧ እርስ በእርስ ፍትጊያ፣ አሳሩን የሚያይበት የግብ ግብ፣ የትንቅንቅ፣ የትልቅልቅ ዘመን፡- ዘመነ - መሳፍንት፡፡ . . . አዎ፣ ያስፈራል፣ ያሳፍራል፣ ያስቆጫል፣ " ኸረ ያገር ያለህ! ኸረ የሰው ያለህ! ኸረ የወንድ ያለህ ያሰኛል!! " የቴዎድሮስ ራዕይ ገጽ፣ 3)

ለውጥ አዲስ ነገርን መሻትን፣ አንድነትን፣ ካለፈው ተምሮ ነገን የተሸለ ማድረግን ይተርካል፡፡ የኢትዩጵያ ሚሊኒየም ሲከበርም ያለፈውን በማስታወስ ፣ መንግስት ያለበትን ሁነት በማሳየት የወደፊቱን ራዕይ ለማሳካት ዝግጅት በማድረግ ነው ይላል። የሚሊኒየሙ አጠቃላይ መሪ ሃሳብ "አዲሱ ሺህ ዓመት የኢትዮጵያን ህዳሴ ያበስራል" የሚል የነገን ራእይ ያነገበ ነው፡፡ (Izabela Orlowska,2023)፡፡ ከዚህ ሃሳብ እና በሚሊኒየሙ ዋዜማ የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ካደረጉት ከላይ ከተገለጸው ንግግር አንጻር ስናስተያየው

የቴዎድሮስ ራዕይ ተውኔት ቁጭትን በተራኪው እንደበት የገለጸበት ነገን መሻትን፣ የተሻለ ሃገር መገንባት ራዕይን ያሳያል ከዚሁ ትይዩ ሁኖ እናገኜዋለን፡፡

" የቴዎድሮስ ራዕይ" ተውኔት ውስጥ ከሚሊኒዬሙ ዝግጅት ጋር ተያይዞ የተንጸባረቀው ሌላኛው ሃሳብ የብሄር ብሄረሰቦች በዓል ነው፡፡ የመጀመሪያው የብሔሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በ1999 ዓ.ም በፌዴሬሽን ምክር ቤት አዘጋጅነት በአዲስ አበባ መከበሩን የፌዴሬሽን ምክር ቤት ድረ ገጽ ይነግረናል፡፡ ሁለተኛው በዓል ደግሞ በኢትዮጵያ ሚሊኒየም በ2000 ዓ.ም በደቡብ ኢትዮጵያ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መዲና በሆነችው ሀዋሳ "ልዩነታችን ውበታችን ውበታችን አንድነታችንና ጥንካሬያችን ነው" በሚል መሪ ሀሳብ ተከብሯል። በጊዜው በስፋት ይንጸባረቅ የነበረው ርዕዮት በአዲስ መልኩ የመጣው የብሄር ብሄረሰቦች በዓል ሲሆን ይህንን በልዩነት ውስጥ ያለ ውበት የሚል መፈክር በሙዚቃዊ ተውኔቱ ውስጥ በተለያዩ የብሄር ብሄረሰብ ሙዚቃ ስልቶች በቀረቡ ሙዚቃዎች ያሳየናል፡፡

በቴዎድሮስ ራዕይ ላይ የቀረበው ሌላኛው በጊዜው የነበረውን ርዕዮተ አለም የሚያንጸባርቀው ሃሳብ አጼ ቴዎድሮስ የልማት አርበኛ ሆነው የተሳሉበት መንገድ ነው፡፡ ልማታዊ ጭብጥን የያዙ ሃሳቦችን እንመልከት፡-

"... በአንድ ሀገር ሃሳብ፣ በአንድ ልብ ፍቅር

እንዋብ አንድ ላይ፣ አንድ ላይ እንምከር

አብረን ከፍ እንበል በልማት እንበልጽግ

እንደገና እናብብ፣ እንደገና እንደግ..." (የቴዎድሮስ ራዕይ ገጽ፣30)

ከላይ በተጠቀሰው መልኩ በቀጥታ በአንድነት ሃገርን በልማት ማሳደግን የሚቀሰቅስ ህብረ ዝማሬን ይጠቀማል፡፡ አጤ ቴዎድሮስ ድላቸውን በአዋጅ በተናገሩበት ወቅት የተጠቀሟቸው ንግግሮችም በተውኔቱ ሲገለጡ የኢሃዴግን ልማታዊ መንግስትነት ቁልፍ ሃሳቦች የሚያንጸባርቁ ሆነው ነው፡፡ የልማታዊ መንግሥት አንዱና ትልቁ መነሻው ኅብረተሰቡ የሚጋራው ልማታዊ ራዕይ ያለው መሆንና ኅብረተሰቡን ለዚህ ራዕይ መሳካት

በተደራጀ መልኩ ማንቀሳቀስ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከምትገኝበት አገራዊ ሁኔታ አኳያ አገሪቱን ከድህነት ማውጣትና ወደ መካካለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ተርታ ማሠለፍ የሚቻለው፣ ሕዝቦች በየአካባቢያቸው ወደ ልማት ማስገባት ሲቻል ነው፡፡

> To enable the whole society to have shared vision with respect to national issues on development and building democratic system and thereby enter the new Ethiopian Millennium with the hope of seeing a better Ethiopia;
>
> To mobilize the society around national development and good governance issues and thereby create national consensus.To promote, through the concerted efforts of the Government and citizens, the national heritage of the country throughout the rest of the world with the view to building the nation's image via-a-vis investment, tourism, trade and other aspects of the country: To convey the country's major national objectives, missions and strategic interests to the society, the youth and the world in general. ( The Ethiopian Millennium Festival National Council Secretariat.)

በጊዜው በነበረው መንግስት መላው ህብረተሰብ በልማትና በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ላይ እንዲቀናጅ በማድረግ ሀገራዊ ጉዳዮችን በማስመልከት ራዕይ ተጋርቶ የተሻለች ኢትዮጵያን ለማየት ተስፋ በማድረግ ወደ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ሚሊኒየም እንዲገባ ማድረግ የሚል ነው የሚሊኒየሙ አከባበር ላይ የተነሳው ከላይ የተገለጸው ሃሳብ፡፡ ይህንን ጭብጥ በተውኔቱ ላይ ተገልጦ እንመለከተዋለን፡፡

> "…የሀገሬ ህዝብ ተእንግዲህ ደስ ይበልህ የአንድነትን ጥቅምና ጉልበት ታውቀዋለህና፤ ተእንግዲህ አንድነትህንና ሰላምህን ጠብቀህ፣
> የሀገርህን ስምና ዝና ለመመለስ በሙያህ ተግተህ ሥራ!!
> - ተእንግዲህ ክርስቲያኑ በክርስቲያንነቱ፣ እስላሙም በእስልምነቱ ፀንቶ፣…

- ተእንግዲህ የመንግሥቱ ሹማምንት ደመወዝ እየተቆረጠላቸው ፡ ይሠራሉ እንጂ ያለደንብ የባላገሩን ጥሪት መቀራመቱን እንዲተው ይሁን፡፡...
- ተንግዲህ ባሪያ - መሸጥና መግዛት በሀገሬ ላይ ፡ ማብቃቱን ሁሉም እንዲያውቅልኝ ሆኖ፤ ይህን ደምብ ጥሶ ሰውን እንደ እቃ ሲሸጥ ወይ ሲገዛ የተገኘም በስቅላት እንዲቀጣ ይሁን፡፡..." (የቴዎድሮስ ራዕይ ገጽ፣37)

የሠቀቀን ደስታ፣ የ.ጨረሻው መጀመሪያ ባለው የቴዎድሮስ ራዕይ ትእይንት ላይም ለልማት ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር እና ለመሳካቱ እየሰሯቸው የነበሩ ስራዎችን ይነግረናል፡፡

ቀደም ሲል በነበረው ትዕይንት ማብቂያ ላይ ይሰማ የነበረው ሙዚቃ እየቀነሰ ይጠፋና፣ በምትኩ ቆየት ያለ የአውሮጳዊያን ሙዚታ ሲምፎኒ / መሰማት ይጀምራል፡፡ መብራት በትንሹ ፈካ ሲል በጋፋት የተሰባሰቡት አውሮጳውያን /እስረኞች በቴዎድሮስ የታዘዙትን፣ መድፍ ሰርተው፣ የሚጓጓዝበትን መንገድ ለመጥረግ የሚያደርጉትን ትግል በሚያሳይ የዳንስ እንቅስቃሴ ይታያሉ፡፡ አፄ
ቴዎድሮስ በአውሮጳውያኑ መሃል እየተዘዋወሩ፣ ሲያበረታቱና በሥራም ሲያግዙ ይስተዋላሉ፡፡ ጥቂት ቆይቶ ዎልዳሚዮር እየተጣደፈ ይገባል፡፡ ሙዚቃው ይቀንሳል፡፡

ዎልዳሚዬር

/በደስታ ስሜት/ ግርማዊ አፄ ቴዎድሮስ የምስራች!

ቴዎድሮስ

ምስር ብላ ከንቲባዬ! ተሳካ? ... አለቀልኝ ሴባስቶፖሌ

ዎልዳሚዬር

ተሳክቷል ጀንሆይ . . . የመድፉ መሽከርከሪያ መንኩራኩር ሥራ መቶ በመቶ ማለት ይቻላል፣ ተጠናቋል፡፡…"

### 3.4.2 ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ "የካሳ ፈረሶች" ታሪካዊ ተውኔት ውስጥ

ስነ-ጽሁፍ ብዙውን ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና አስተሳሰቦች ያንጸባርቃል። ደራሲያን በሥራቸው ላይ ያሉትን ማህበራዊ ደንቦችን፣ የፖለቲካ እምነቶችን እና ባህላዊ እሴቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ፣ ይህም ስለ ታሪካዊው ሁኔታ ግንዛቤን ይሰጣል። በሥነ ጽሑፍ ንድፈ-ሐሳብ፣ በተለይም ከሐዲስ የታሪክ አመለካከት አንፃር፣ ርዕዮተ ዓለም የሚያመለክተው የእምነት፣ የእሴቶች እና የአስተሳሰብ ማዕከሎችን ነው። ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች በዙሪያቸው ያለውን ዓለም የሚረዱበትን እና የሚተረጉሙት መንገድ ይመለከታል። (Greenblatt፣1980)፡፡

እንዲህ አይነቱ ታሪካዊ የሃገር ክህደት ውርስ በኢሃዴግ ዘመንም ተላልፎ መተማ እና ቋራ ለሱዳን በመንግስት ይሁንታ እና ፈቃድ ተላልፎ መሰጠቱን ተራኪው የትውልድ ቦታቸውን ለመጎብኘት ለፈለጉት ቴዎድሮስ ያረዳቸዋል።

"…አዎ ድሮ የምታውቋት ኢትዮጵያ እንደፊተኛው ዘመን አይደለችም፡፡ ተቆራርሟ አልቃለች፤ ተቦትርፋ፣ ተቦረታትፋ መጠኗ እያነሰ

ነው፤ ይላሉ፡፡

ካሣ፤ ምንድነው ምንሰማው? አገሪቷ መሪም የላት? ማንነው ቆርሶ

ሰጭ? [ወደተራኪው ዞረው] መንግስት ምን አለ?

ተራኪው! መንግስት መሬቱ ቀድሞውንም ቢሆን የሱዳኖች ነው ብሎ፤ ነባር የቋራ ነዋሪዎችን አፈናቅሎ መሬቱን ቆርሶ ድርሻችሁ ነው ብሎ

ሲሰጣቸው የአካባቢው አርበኞች ደግሞ መሬታችንን አናስቆርስም በማለት እየተሟገቱ ነው አሉ!..." (የካሳ ፈረሶች ገጽ፣ 259)

የ"የካሳ ፈረሶች" ታሪካዊ ተውኔት በዘመኑ የነበረውን ማህበረ ፖለቲካዊ ሁነት በማንጸባረቅ የቀደመው ስርአት የወለደውን የብሄር ክፍፍሉን ይሳለቅበታል። ብሔርተኝነት ይልቅ የኢትዮጵያዊነት ስሜትን ያዳብራል። በአብይ ዘመን እንዲህ ያለ ትረካ ተቀባይነት አለው ስለ አገራዊ አንድነት የራሱን ሃቲት ያስተጋባል። ተውኔቱ የአጼ ቴዎድሮስን የአንድነት ምሰሌነት. ጀግንነት እና ዘመናዊነትን በማጉላት በአብይ ዘመን የነበረውን የመንግስት አጀንዳን ያስተጋባል፡፡

ተውኔቱ የሽግግሩን ጊዜ ትርክቶች እና የሚያንፅባርቅም ነው። የመደመር ፍልስፍና ከቴዎድሮስ አንድ ኢትዮጵያን የመፍጠር ራዕይ ጋር የተቆራኘ ነው። የኢሃዲግን አመራር በመቃውምም የተገነባውን ያፈርሳል። ከነዚህ ትዕይንቶች መካከል ለአብነት ብናነሳ የስልጣን ሽግግሩን እና የአጤ ዩሃንስን ክህደት ያነሳል። ይሄ ደገሞ በአማራ እና በትግራይ ልሂቃን መካከል ያለውን እሰጣ ገባና የኢሃዴግ ዘመን የተሳሳቱ የሚባሉ አካሄዶችን የሚተች ነው።

> "...ባላምባራስነት አነሰኝ ብሎ ሰበብ ፈልጎ ይሸፍትብዎ እንጂ፣ ጉዳይዋ እንኳን ሌላ ነው የምትመስለኝ። ታዲያ ጄኔራል ናፒርን መንገድ እየመራ፣ በቆነጃጅትና በጫማ፣ በጠጅ እና በአዝማሪ ጋጋታ እያስነዳ እርስዎን አሳልፎ ለመስጠት የሚያስችል ምን ተገኜ? አይመስልዎትም?...።" (የካሳ ፈረሶች ገጽ፣245)

አጤ ዩሃንስ ቂም ቋጥረው ቴዎድሮስን አሳልፈው እንደሰጡት ይነግረናል።

> "... ደጅ አዝማች ንጉሴ እኮ እርስዎን ከገጠመዎት ሽፍታ ሁሉ የተለየ ነበር። ሰምተዋል አይደል፣ የትግራይ ገዢ በነበረ ጊዜ፤ ለፈረንሳይ ንጉሥ ለናፖሊዮን እንዲህ ብሎ መፃፉን? 'አባቴ ይሁኑ እኔም ልጅ እሆንዎታለሁ

አሁን አንድ ሽፍታ ንጉስ ተነስቶ እኔን በማጥቃት ላይ ነው። ... እንደእውቀትዎ ይርዱኝ' ብሎ አልነበር?

እርስዎም ሆኑ በእርስዎ ዘመን የነበሩ መሪዎች፤ ከአገራችን ባንዲራ ውጭ የባዕድ አገር ባንዲራ በየአደባባዩ እንዲውለበለብ አይፈቅዱም ነበረ፡፡ደጃዝማች ንጉሴ ግን በትግራይ ምድር የፈረንሣይ ባንዲራ እንዲውለበለብ ፈቅዶ ነበርኮ ከአገሪቱ የተወሰነውን ክፍል ቆርሶ ለመሸጥ ስለተደራደረው ስለዚህ ሰው ምነው ምንም አለማለታቸው?..." (የካሳ ፈረሶች ገጽ፣245)

## 3.5 የኃይል ተለዋዋጭነት

### 3.5.1 የኃይል ተለዋዋጭነት "የቴዎድሮስ ራዕይ" ተውኔት ውስጥ

የሐዲስ ታሪክ ስነ ጽሁፋዊ ሂስ ሊቃውንት በሥነ ጽሑፍ እና በታሪክ መካከል ያለውን ግንኙነት እርስ በእርሱ የተቆራኘ አንዱ ሌላው ላይ ተጽእኖን የሚያሳድር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ስነ-ጽሁፍ የታሪክ ነጸብራቅ ብቻ ሳይሆን ታሪክን የሚቀረጽ እና የሚቀረጽውም በታሪካዊ ሃይሎች ነው ይላሉ። ሃይል ቀጣይነት ያለው ዕውቀት፣ ዕውቀትም ቀጣይነት ያለው ሃይል ነው ይላል ፉኮ፡፡ እውቀት ሁል ጊዜ የሃያላንን ቦታ እንደሚደግፍ እና እውቀትም በኃይል መዋቅሮች ውስጥ የተፈጠረ ነው፡፡ ኃይልን በተፈጥሮው ያልተማከለ፣ የተንሰራፋ ብቻ ሳይሆን ከታች ሆኖ የሚሰራ እና በሁሉም የማህበራዊ ግንኙነት እና የእውቀት ምርት ውስጥ የሚሰራጭ አድርጎታል። (Foucault,1980)፡፡

"ቴዎድሮስ ራዕይ" ተውኔት ውስጥ ሃይል ምን ያህል ተለዋዋጭ እንደሆነ እናያለን፡፡ አነሳሳቸውን በተረከበት ክፍልም

ተራኪ

" እነካሳ ናቸው፡፡ . . . በገዛ አገራቸው መጠቃቱ፣ መገፋቱ ቢያስከፋቸው የሃገራቸው መከራ፣ የወገናቸው ፍዳ ከያሉበት ሁሉንም አፈላልጎ፣ . . .(ቴዎድሮስ ራዕይ፣ 5)

የተነሱት እንዲህ ተሰባስበው በመሸፈት መሆኑን ይነግረናል፡፡ ገብርየ ለወደዳት የማር ውሃ፣ ካሳም ለተዋቡ በዘራቸው አማካኝነት ለጋብቻ አይመጥኑም ተብለው የጥላቻው ገፈት ቀማሽ ሆነዋል፡፡ ይህ የባላባቶች ጊዜም ከቴዎድሮስ መነሳት በኃላ ይታገሳል፡፡

ቴዎድሮስ ከምንም ነገር በላይ አጥብቀው የሻቱት እውቀትን ነው፡፡ ከንግስት ቪክቶሪያም ደጋግመው የሚጠይቁት በደብዳቤ እውቀትን የሚያስቀስማቸው ሰው ነው፡፡ መጨረሻቸውም የሻቱትን እውቀት በኃይል ለማስመለስ ሲጥሩ ነው፡፡

ቴዎድሮስ

የንግስት ቪክቶርያ ቸልታ ከአንድ የሰለጠነች አገር፣ የሰለጠነች ንግስት የሚጠበቅ . . .

እንደኔ ላለ፣ በሃገሩ ህዝብ ልቦና ድንቁርናና ሰይጣን ነግሰው፣ የገዛ ወገኑ አልሰማህም ላለው፣ የገንዛ ወገኑ አልሰማህም ላለው፣ የገዛ ዘሩ ባዳው ሆኖ፣ በዚህ ሲሰበስበው፣

በዚህ እየተበተበ አሳሩን ለሚያሳየው፣ . . . አንድ ንጉስ የተገባ ምላሽ ነው?

አውሮፓውያኑ

አይደለም ንጉስ ቴዎድሮስ

ቴዎድሮስ

እስኪ እንግዲህ ይታያችሁ! . . . ድንቁርናና ሰይጣን በልቦናው ቢነግሱ እንጂ የሃገሬ ሰው የሚያስከፋ ምን ጥፋት ሰራሁ? . . . "ቴዎድሮስ ራዕይ"

በተውኔቱ ውስጥ አጼ ቴዎድሮስ እንዲህ ህዝባቸውን የሚወቅሱበት ክፍል ካለመማሩ ካለማወቁ የመጣ እንደሆነ የሚገልጹበትን መንገድ ኢህአዴግ በዘመኑ ከላይ ያነሳሁትን አገላለጽ የሚያጠናክር ነው፡፡ ኢህአዴግ  የገጠሩ አርሶ አደር የራሱን እጣ ፈንታ ለመወሰን ብቁ ያልሆነና በተቃራኒው ‘ያልተማረ ’፣በ ‘ ኪራይ ሰብሳቢዎች ’ ለመጭበርበር ተጋላጭ

የሆነና በዚህም ምክንያት የመንግሥት 'ጥበቃ ' እንደሚያሻው ተደርጎ ይቆጠራል (Lefort, 2013)፡፡

### 3.5.2 የኃይል ተለዋዋጭነት "የካሣ ፈረሶች" ተውኔት ውስጥ

ስነ-ጽሁፍ ስራዎች የታሪካዊ ሁኔታዎች ነጸብራቆች ብቻ ሳይሆኑ የማህበራዊ ሃይል የሚዘዋወርበት እና የሚቀየርባቸው የድርድር እና የመለዋወጫ ስፍራዎች ናቸው። ይህ የተገላቢጦሽ ሞዴል የኃይል ግንኙነቶችን በመገንባት፣ በማጠናከር እና አንዳንዴም በማፍረስ ላይ ስነ-ጽሑፋዊ ጽሑፎች ይሳተፋሉ። (Veeser, H.1994)

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ስነ-ጽሁፍ አሁን ያሉትን የሃይል አወቃቀሮች እንዴት እንደሚያጠናክር ወይም እንደሚገለባበጥ እና ለእውቀትና ርዕዮተ አለም ስርጭት እንዴት አስተዋፅኦ እንዳለው ይመረምራል፡፡ ሐዲስ ታሪካዊነት በመሠረታዊ መልኩ በሥነ ጽሑፍ፣ በታሪካዊ አውድ፣ እና በኃይል ግንኙነቶች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት መረዳት እንዳለብን መሰረት ጥሏል፡፡ ታሪክ የማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን የስነጽሁፍም ተመጋጋቢ ውጤት ነው፡፡ የስነ ጽሁፍ ስራዎች በተፈጠሩበት ዘመን ያለው ማህበራዊ ፖለቲካዊ አውድ ነጸብራቆች ናቸው፡፡ (pietruszynski, 2006)፡፡

ከዚህ ንድፈ ሃሳብ አንጻር የኃይል ተለዋዋጭነት እንዴት በተውኔቶቹ ውስጥ እንደተወከለ ስንመለከት በኢህአዴግ ዘመን የነበረው ትረካ ከላይ ወደታች የሚወርድ ቁጥጥር የበዛበት ነው፡፡ ለምሳሌ፡-

> "…ካሳ፤ ሊመስል ይችላል፤ የኔ ጥያቄ አሁን ቀጥለን በምናየው ቴአትር ውስጥ የዩሐንስ ሚና ለምን ተገደፈ ነው?
>
> ተራኪው፤ ቴአትሩ የተጻፈበት ዘመን ስለ አጼ ዩሐንስ ክህደት እንደ ልብ የማያናግር ሆኖ አገኝቶት ይመስለኛል" (የካሣ ፈረሶች፣ 245 )

ከላይ በተገለጸው መንገድም ኃይልን የተቆጣጠረው አካል ታሪክ ነገራን በፈቀደው መልኩ ይቆጣጠረው እንደነበር ይገልጸል፡፡ በኃላም ኃይል በተለወጠ እና የኢሃአዴግ ማብቃት ተከትሎ ተውኔቱ ውስጥ አጤ ዩሃንስ የባንዳነት ተግባር እንደፈጸሙ እንዲህ ይነግረናል፡፡

… ተዋበች፣ … አሁን በጠቀስከው ቴአትር ውስጥም አጼ ዮሐነወስ የለም? መንበሮቻችንን እንዴት እንደተነጣጠቅን፣ አልጋዎቻችንን እንዴት እንደተወሳሰድን ማሳየቱ ምን የሚያጌድለው ነገር አለ? ከኛ ቀጥሎ ለመጣው ትውልድ የምናስተመወረው ነገር ነበርኮ! በርግጥ እኔን በተረዳሁት ሁኔታ አይጽፉትም ይሆናል፡፡ በነገራችን ላይ ዮሐንስ እና ምኒልክ ከርስዎ እግር ስር ሆነው ማደጋቸው የታወቀ ነው፡፡ እንደሚባለው እርስዎ ምኒልክም ደጃዝማች ማድረግዎ፣ እሱን ደግሞ ባላምባራስ በመሰኘቱ ቅር ተሰኝቶ ብቻ አይመስለኝም፤ በእርስዎ ላይ ቂም ይዞ የሸፈተ፡፡ ከጠላትዎ ጋር አብሮ መንገድ መርቶ የተገኔ፡፡ (የካሳ ፈረሶች፣ 244)

ታሪክ ኃይል ባለቸው ሰዎች ይፈጠራል ወጥ ሳይሆን ተለዋዋጭ ነው የሚለውን ሃሳብ በእነዚህ ሃሳቦች ይታያል፡፡

### 3.6 ዘመኑ በተውኔቶቹ ውስጥ ያሳደረው ተጽዕኖ

ሐዲስ ታሪካዊ ሂስ ጽሁፎች በዘመናቸው ተጽዕኖ ያድርባቸዋል ብሎ ያምናል፡፡ ከዚህ አንጻር "የቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ "የካሣ ፈረሶች" ሁለቱም ተውኔቶች ውስጥ በዘመኑ የነበረው ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አውድም ሆነ ርዕዮተ አለም ስንመለከተው ተጽዕኖው በጉልህ ይታያል፡፡ ለምሳሌ:- "የቴዎድሮስ ራዕይ" ተውኔት ውስጥ በዘመኑ የነበረው ሁነት በገጸ ባህርያቱ ውስጥ እንዴት እንደተንጸባረቀ እንመልከት፡፡

ቴዎድሮስ ለኢትዮጲያ ከፍታ፣ ለህዝቦች መብት እኩልነት እና ለዘመናዊነቷ መስዋዕትነት የከፈሉ ያደርጋቸዋል፡፡ የሙዚቃዊ ተውኔቱ የመጨረሻ ትዕይንት ላይ

/ በጨለማው ውስጥ ጎልቶ በሚሰማው ዕልልታ ላይ ተደርቦ፣ የቴዎድሮስ ራዕይ የሚለው ደማቅ ህብረ ዝማሬያዊ የመዝጊያ ሙዚቃ መሰማት ይጀምራል፡፡ ተወዛዋገሮችና ድምጻውያን በጠቅላላ፣ የተለያዩ የኢትዮጲያ ብሄር ብሄረሰቦችን አልባሳት በመልበስ፣ እያንዳንዳቸው፣ አንድ አንድ የተለኮሰ ጧፍ በመያዝ፣ በተራ በተራ እየገቡ፣ በወደቀው የቴዎድሮስ አካል ዙሪያ ክብ እየሰሩ ይቆማሉ፡፡/

የቴዎድሮስ ራዕይ /ህብረ- ዝማሬ/

አንድ ነው፡-

አንድ እውነት መስካሪ

አንድ ነው፡-

አንድ እውነት ዘካሪ… (የቴዎድሮስ ራዕይ፣ 56)

"የካሳ ፈረሶች" ተውኔት ላይም ይህንን የቴዎድሮስ ራዕይ ላይ የተገለጸበትን መንገድ ሲገልጽ

> ካሳ፤ (ቱግ ብለው) ተሸራርፈን ልናልቅ እኮ ነው ጎበዝ፡፡ ምን እየተደረገብኝ እንደሆነ ልብ ብላችኋል? ግርማቸው ተክለኃዋርያት ለቀዳማዊ ኃለስላሴ ባህሪይ እና አገዛዝ እንዲመች አድርርግ፣ ዘውዳዊ ስርአትን አጎናጽፎ ከቀረጸኝ፣ ጸጋዬ ገብረመድህን ለመንግስቱ ኃይለማርያም ባህሪይ አስማምቶ፣ ወታደራዊ ባህሪይ አልብሶ ከቀረጸኝ… የጌትነት እንየው ደግሞ እናየው የለ… ይህን ጊዜ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት ለማስጠበቅ የሸፈተ፣ ጫካ የገባ ነው ብሎኝ ይሆናል… ( የካሳ ፈረሶች 245)

ተውኔቶቹ በተቀረጹበት ዘመን የነበረው ርዕዮተ አለምም ሆነ ማህበረ ፓለቲካዊ አውድ በተውኔቶ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያሳያል፡፡

## 3.7 የተውኔቶቹ አንድነት እና ልዩነት

የ "ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ "ካሣ ፈረሶች" ሁለቱም ተውኔቶች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስማቸው ጎልቶ የሚነሳውን ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ንጉሰ ነገስት በኢትዮጰያ ህይወት እና ትሩፋት ጋር በጥልቀት የተሳሰሩ ቢሆንም ይህን የሚያደርጉት ግን በተለያየ እይታ ነው።

ሁለቱም ተውኔቶች በቴዎድሮስ ዘመን የኢትዮጵያን የአንድነት ትግል የክልላዊ የጦር አበጋዞች በየአካባቢው ማመፅን እና የውጭ ስጋቶችን የሚያሳዩ ናቸው። የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" ንጉሰ ነገስቱን በአንድነት ኢትዮጵያን የመመስረት ህልሙ በክህደት እና በቅኝ ግዛት የከሸፈበት ጀግና ሰው አድርጎ ያቀርበዋል ። የ"ካሳ ፈረሶች" ደግሞ ቴዎድሮስን በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ እያሳየን የዘመኑን ፖለቲካ ለመተቸት ፌዝ በመጠቀም እውነተኛ አንድነት ይቻል እንደነበር ያጠይቃል። በአንጻሩ የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" ውድቀቱን የማይቀር እና አሳዛኝ አድርጎታል። የ "ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ "ካሣ ፈረሶች" ሁለቱም ተውኔቶች ታሪክ እንዴት እንደሚታወስ ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ የ"ካሳ ፈረሶች" የሚጋጩ የቴዎድሮስን ስራቶች (ጀግና እና አምባገነንነት) ለማሳየት ሜታ ቴአትርን (በድራማ ላይ ድራማን) ይጠቀማል።

> ተዋበች፣ ይሄ ምኑ ያሰደስታል ካሳ? እንደ ደጃች ብሩ ባሉ ክፉ ሰው ላይ የወሰዱት እርምጃ አንጀት አርስ ነበር፡፡ የጎጃምን ህዝብ እንደ ደጃች ብሩን የሚያህል ትዕቢተኛ ገዥ ከአናቱ ላይ አንስተው ወደ መቅደላ በመወርወር እድሜ ልኩን ሊያመሰግንዎ ይገባል ፣ . . . ተዋበች፣ የሰው አገር ሰውን እንዲህ አሳር ማብላት ምን ይረባል፣ በሰውም ዘንድ አያስመሰግን፣ በእግዜርም ዘንድ አያስኮራ … የካሳ ፈረሶች፣248 )

የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" ደግሞ የበለጠ ባህላዊ፣ ጀግንነት ያለው ትረካ ይነግረናል፡፡

> ” . . .ተራኪ
>
> ማን እንበልህ?. . .
>
> እስከ ባህር ማዶ ግዛት ታሰፋለህ
>
> ሰላምና ስርአት በአገር ታሰፍናለህ
>
> አንተ ዳግማዊ ካሌብ ስምህን ማን እንበል?”

የ"ካሳ ፈረሶች" የቴዎድሮስ ታሪካዊ ውርስ በጥቅም ላይ እንደዋለ በመጥቀስ ስለ ታላላቅ ታሪካዊ ትረካዎች እውነተኛነት ታዳሚዊ እንዲጠይቅ ከማድረግ ባሻገር የተወሳበትን መንገድ ይሞግታል ያልተነሱትንም ይጠቁማል፡፡ የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" በተቃራኒው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ጠባቂ ሰማዕት አድርጎ ያቀርባቸዋል፡፡

"የካሳ ፈረሶች"

የ "ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ "ካሣ ፈረሶች" ሁለቱም ተውኔቶች አጉልተው ቴዎድሮስ በአውሮፓ ኃያላን በተለይም በብሪታንያ ላይ ያሳየውን እምቢተኝነት ያሳያሉ። የ"ካሳ ፈረሶች" በመቅደላ (1868) የተፈጠረውን በማጉላት ደፋር እና ጀግንነቱን ሲያሳይ

". . . ተዋበች፣ . . . ኸይ አባ ታጠቅ ወንድ ነዎትኮ!

ካሳ፣ በሚስት አይን አይተሸኝ ነዋ!

ተዋበች፣ አገር ሲመሰክር የምንሰማውን!(የካሳ ፈረሶች)

የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" ደግሞ የዲፕሎማሲያዊ ጥረቱን (ለምሳሌ ለንግሥት ቪክቶሪያ በተደጋጋሚ የተላኩ ደብዳቤዎች) እና ወታደራዊ ተቃውሞውን አፅንዖት ይሰጣል፡፡

የቴዎድሮስ ደብዳቤ

" . . .ቱርኮች በባህር ላይ ሆነው፣ መልዕክተኛየን አናሳልፍም ብለው ቸግሮኝ ሳለ ቆንስል ካሜሮን ቢመጣልኝ . . . በእጅጉ ደስ አለኝ፡፡ የደስታዬ ዋናው ምክንያት የላኩት መልዕክቴ የንግስትን አፋጣኝ ምላሽ በቆንስል ካሜሩን በኩል እንደሚያደርሱኝ መተማመኔ ነው፡፡ " (የቴዎድሮስ ራዕይ, 37)

የ "ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ "ካሣ ፈረሶች" በትረካ አቀራረባቸው የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" ጀግና፣ አምባገነን እና አሳዛኝ ሰው አድርጎ ይገልፃቸዋል። ታሪካዊ ክስተቶች የተቀናጁ ፍሰት ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ ናቸው። የ"ካሳ ፈረሶች" ታሪክ እንዴት እንደሚዘጋጅ፣ እንደገና እንደሚፃፍ፣ እና ፖለቲካዊ እንደሚሆን በማሳየት በታሪክ ነገራችን ይሳለቃል። ገፅ

ባህሪያትን (ቴዎድሮስን ጨምሮ) ለታዳሚው ንግግር በማድረግ ታሪክን ለመተርጎም ተባባሪ ያደርጋቸዋል። የቴዎድሮስን ዘመን ከዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ጋር ያነፃፅራል።

የ"ቴዎድሮስ ራዕይ" የሶስት ድርጊቶች ውጤት ያደርገዋል። ግልፅ የሆነ መነሳት፣ ንግስና እና ውድቀትን የያዘ ነው። አገራዊ ማንነትን ለማነሳየት ያለፈ ታሪክን ሲገነባ በአንፃሩ "የካሳ ፈረሶች" ታሪክ የተገነባበትን መንገድ ያፈርሳል ይህም ኃይል የማህደረ ትውስታን እንዴት እንደሚቀርፅ ያሳያል። እነዚህ ልዩነቶች ተውኔት እንዴት ታሪካዊ ተረኮችን ማጠናከር ወይንም መቃወም እንደሚችል ያሳያሉ።

ስለዚህ፣ እነዚህ ድራማዎች አዲሱን ተረክ ከመቀልበስ ይልቅ፣ ታሪካዊ ፍቅርን በመጠቀም የሀገር ፍቅር ርዕዮተ ዓለምን ለማጠናከር በአብዛኛው ያጠናክሩታል። በአንድነት፣ በእድገት እና በኩሩ ብሔርተኝነት ላይ የተመሰረተ የኢትዮጵያዊነት ራዕይን እንድንከተል ይገፋል፡፡

"የካሳ ፈረሶች "ተውኔቱ የሽግግር ርዕዮተ ዓለም ነጸብራቅን ያለፉ ታሪካዊ ቅራኔዎችን መፍታትን ያሳያል። የቴዎድሮስ ትሩፋት በመስዋዕትነት ወይንስ በደም እና በዓመፅ ላይ ነው የሚወሳው? ተውኔቱ የጋራ ማንነትን እንደገና ለመገንባት የታሪክ ጉዳትን እንደገና እንዲመረምር ያስገድዳል።

> "...ካሣ፤ ማን አልከን ርዕሱን?
>
> ተራኪው፣ የቴዎድሮስ ዕንባ፡፡
>
> ካሣ፤ ዕንባ? የቴዎድሮስ ዕንባ? [ግር አላቸው፤ ቅርም አላቸው፡፡] ዕንባን ደግሞ _ ምናመጣው?ያገሬን ታሪክ በደሜ ነው እንጂ በዕንባዬ
>
> አይደለም የጻፍኩት፡፡ በደሜ የጻፍኩትን ታሪክ ልታነቡ ባትችሉ እንኳን፣ የላቤን ውለታ እንደምን ተዘንግቷችሁ ነው- ዕንባዬ ላይ ማተኮራችሁ? እንባዬ ላይ ከማተኮር በደሜ የፃፍኩትን ታሪክ በትክክል ብታስተላልፉት። (የካሳ ፈረሶች ገጽ፣ 231)

በዚህ ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ በ"ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ"የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ በተሰኜ ጥናት ተውኔቶቹ ውስጥ የተፈጠሩበት ዘመን የነበረው የሃይል ክፍፍል እና ርዕዮተ

አለም፣ በዘመኑ የነበረው ማህበረ ፖለቲካዊ ሁነት ተጽዕኖ አሳድሮባቸዋል፡፡ በትንተናው ለማየት እንደተሞከረው አጤ ቴዎድሮስ በተውኔቶቹ ውስጥ በተፈጠሩበት ዘመን የነበረው ርዕዮት አራማጅ ተደርገው ተገልጸዋል፡፡ ይህም ከሃዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ ታሪክ በተፈጠረበት ዘመን ተጽዕኖ ይደረግበታል እሱም ተጽዕኖ ያደርጋል የሚለውን ያረጋገጠ ነው፡፡

## ምዕራፍ አራት፡- ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ተውኔት ታሪካዊ ምሳሌዎችን ከወቅታዊ ሁነቶች ጋር በማዋሃድ ለህብረተሰቡ ለውጦች እንደ መስታወት ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል። ይህ ጥናት ሐዲስ ታሪካዊ ንባብ በ"ቴዎድሮስ ራዕይ" እና በ"የካሳ ፈረሶች" ተውኔቶች ውስጥ ያደረገ ሲሆን በተውኔቶቹ በተፈጠሩበት ጊዜ የነበረው የሃይል ተለዋዋጭነት እና ርዕዮተ አለም፣ ማህበረ ፓለቲካዊ ሁነትን በአጼ ቴዎድሮስ ውስጥ ያሉ ጭብጦችን በማንሳት እና በተጻፉበት ዘመን የነበሩት ሁነቶች እንዴት ተውኔቶቹ ላይ ተንጸባርቀው በዳግማዊ ቴዎድሮስ ላይ ያለንን እይታ ቀረጹት የሚለውን ለማየት ሞክሯል፡፡ ይህም ስነ-ጽሁፋዊ ጽሑፎችን ከሚፈጠሩት የሃይል አወቃቀሮች የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ያሳያል። የዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስን የተወከሉበትን መንገድ በመመርመር ጥናቱ የመንግስትን አስተሳሰቦች እንዴት እንደሚያንጸባርቁ፣ እንደሚያጠናክሩ ወይም እንደሚቃወሙ ተመልክቷል።

በግኝቱም እነዚህ ስራዎች በተፈጠሩበት ጊዜ የነበረው የሃይል ተለዋዋጭነት እና ርዕዮተ አለም፣ ማህበረ ፓለቲካዊ ሁነት እንደተንጸባረቀባቸው ማጤን ተችሏል። በጥናቱ የተካተቱት ግኝቶችም እንደሚያሳዩት ጽሁፉን በተፈጠረበት አውድ ውስጥ በማስቀመጥ በአጼ ቴዎድሮስ ዙሪያ በታሪክ ምክንያት ለሚነሱ ውዝግቦች እና ግጭቶች መፍትሄ እንደሚሆን ነው፡፡ ታሪክ ተለዋዋጭ በመሆኑ እና ስነፅሁፍን የዘመኑ ፖለቲካ እና ርዕዮተ ዓለም ተጽዕኖ ስለሚያሳድርበት ታሪካዊ ጽሁፎችን ለመረዳት የተፈጠሩበትን አውድ መመርመር እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡

## ዋቢ መጻሃፍት


ጎሩት አድማሱ (ዶ/ር)፡፡ 2014፡፡ ታሪካዊ እውነት አቀራረብ ‹‹በቴዎድሮስ ራዕይ››፡፡ ባህርዳር፣ ባህርዳር ዩንቨርስቲ

መስፍን ወልደማርያም (ፕሮፌሰር)፡፡ 2005፡፡ መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ

ተክለጻዲቅ መኩሪያ፡፡ 1928፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ባህሩ ዘውዴ፡፡ (1999) የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ከ1847 እስከ1983፡፡ አዲስ አበባ፣ አአዩ ማተሚያ ቤት፡፡

አለቃ ወልደማርያም ዘሸዋ፡፡ 1897፡፡ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ታሪክ፡፡ፓሪስ፣ ሙሴ ጊልሞቶ

አብዱልጀሊል አሊ፡፡2022፡፡ ኪነት ያገነነው አጼ፡፡ በማን ማተሚያ ቤት እና የት እንደታተመ አይገልጽም፡፡

አያልነህ ሙላቱ፡፡ 1997፡፡ የሥነጽሁ ፍቅኝት፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት

እንዳለጌታ ከበደ፡፡2009፡፡ ያልተቀበልናቸው፡፡ የካሳ ፈረሶች፣ አዲስ አበባ፣ እታፍዘር አሳታሚዎች

እጥፍወርቂ አደመ፡፡(2000)፡፡ “የቴዎዴሮስ ራዕይ ታሪካዊ ዴራማ”፣ “እቴጌ ጣይቱ ታሪካዊ ዴራማ” እና “ወይ አዲስ አበባ ድራማ” ከታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ተውኔት አኳያ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍሌ ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ያልታተመ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ 2007፡፡ የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ አዲስአበባ፣ ማህሌት አሳታሚ ድርጅት

ጌትነት እንየው፡፡ 2000፡፡ የቴዎድሮስ ራዕይ፡፡ አዲስ አበባ፣ ያልታተመ የተውኔት ፅሁፍ

ያለው እንዳወቀ (ዶ/ር) ፡፡ 1998 የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ አዲስአበባ፣ አዲስ አበባ ፕረስ፡፡

ጳውሎስ ኞኞ፡፡ 1985፡፡ አጼ ቴወድሮስ፡፡ አዲስአበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት

Alemseged Tesfai.(2003). Identity Jilted: Reimagining Identity in Ethiopia. Red Sea Press.

Bhabha, H. (1994). The Location of Culture. Routledge.

Greenblatt, S. (1988). Shakespearean Negotiations. University of California Press.

Greenblatt, Stephen, and Michael Payne. 2005. the greenblatt reader. Uk. Blackwell Pub.

Izabela anna Orlowska, (2023) Forging a nation: The Ethiopian millennium celebration and the multiethnic state Ethiopia

Messing S.D. 1960). A Modern Ethiopian Play: Self Study in Culture Change Anthropological Quarterly

Montrose, L. (1989). “The Poetics and Politics of Culture.” New Historicism, Veeser (ed.)

Nebiyu Biyu, Presentation and Representation of History in ‘‘Etege Taytu’’ and ‘‘YeTewodros Raey’’. Addis Abeba university Theater dipartement A thesis presented fulfillment of degree master of art in literature (English).

Richard A. Caulk. 1972. Religion and the state in Nineteenth Cenetury Ethiopia, Journal of Ethiopian studies, Vol. X, n.1, Addis baba.

Richard Pankhurst. 1985. History of Ethiopian Towns from the Mid- Ninteenth Century to 1935. Stuttgart

Taye Assefa.1980. Tewodros in historical fiction. A thesis presented to the school of graduate studies Addis Abeba University in partial fulfillment of requirement for the degree master of art in literature (English).

Tyson Lois. 2006. Critical Theory Today: A User-Friendly Guide. New York: Routledge.